ሐቀኛ ተራግጂች ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለንደብ እሁኑት እንጓለቀቁ የሚጠይቁትና የሚታገ ቱት ለዚህ መሠረታዊና ኢብቮት ተግ ባር ነው። አሁን ባለንበት ሁኔታ የዘህ መብት መለቀቅ የሕዝቡን የመፍጠርና ውስብስብ ችግሮችን የመፍታት ችሎታ ለማንቀሳቀስ ያስችላል። ሰፈው ሕዝብ በአለቦቱና በአገሪቱ ችግሮች ላይ በዓደዛባይ የመሣኸር መብት አስ ከፈለው ድረስ ሰፈው ሕዝብ ተአምር ሰፈ ነው ፣ የታሪክ አደራጊም ፈጣሪም ሰፈው ሕዝብ ነው የሚለውን ሐሪገ ያባለ ግፋ ብኖገጠውየል ምንም አይ ረባንም። አዚህ ላይ እንድ ምሳሌ መጠ

ቀስ ይበቃል። በአካባቢው አደጋሪ ምች የከፈቀብንን ግልፅ መርነትና የተ ገንጣይ ድርጅቶችን ዓመፅ ለማከሸፍና ቁጥሩ ፲፯ሺህ የሆነን ሰው የመፍጠርና ውስብስብ ችግሮችን የመፍታት ችሎታ ለማንቀሳቀስ ቢቻል ኖሮ የሰ ግሊያ ወረራ እንዳህ ሳይነት አደጋ ላይ ባልሳለን ነበር።

ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ የሚለውን አቋም ትናንት ሲታገሉለትና ሲከራከሩለት ቆይተው ዛሬም እንዳንሸሻው ወይም ምን እንዳ ገኙ ሳይታወቅ መልሰው የሚጥሉት የገብረቱ ድርጅቶች እርስ በርሳቸው የሚታረኑና መያሸያ መጨበጫያ የሌላቸው እደናጋሪ ቃሎች መወራ ወር ይከዋል። (በነገራችን ላይ ጥቂ ቶች ያኔ ተሳስተን ነበር ይሉ ገብተ ዋል። በዚያ እያያዝ የብሔራዊ ዲሞ ክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም የአገራ ችንን ሕዝቦች ትግል መሠሪያ መሆኑ በስሠተት ነው የሚል እንዳይከሰልና የባስ አሳብ ውስጥ እንዳገባ ያስጋል)።

፩- ዲሞክራሲያዊ መብቶቹን ለጭቁኖች ያለገደብ እሁኑት ማለት የመንግሥት ሥልጣን መጠየት ነው።

ይሆንን መከራከሪያ የሚያቀርቡት ወይ ሀቀኝነትና ቅንነት የጐደላቸው ናቸው። አልያም የማርክሲንም አቡ ጊዳን ጥና የቅጠሩ(ምናልባትም መርሐ ግብሩ—የገብረቱ ከተንደረ በሳላ) ናቸው።

እነርሱ የሚሉት ፡—

፩- ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁ ኖች ያለገደብ የሚረጋገጠው ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ስትገነባ ነው። ደርግ ደግሞ የጭቁኖችን እምባ ሰን መንግሥት የሚያረጋግጥ አይደ ለም።

፪- ይህ መብት እሁኑት ይለቀቅ ግለት ደግሞ ሕዝቡ ነቅቷል ፤ተደራጅ ቷል ፣ ታጥቋል የመንግሥት ሥልጣን ለይዟ ይችላል ግለት ነው ይላሉ። ፫- እነኝህ በአድርባይነት ያጮብደዱ ሁሉ ሆነ ሰፈው ሕዝብ «ዲሞክራሲ፣ ዲሞክራሲ» እያለ ጊዜያዊ ወታደራዊ ወገ መንግሥት ስንጓያስቸገርባቸው ሲሉ የመሰዴት አቋም ከኢ-ሕ-አፓ ጋር

በግራና በቀኝ የረሙ የተገናኙት እነ ርሱ እንጂ ሐቀኛ ተራግጂች አንሳል ሆነ መከራከሪያያቸው ግልፅ ያደርጋል። ከአንደ ዓመት በላይ የታገሉለትንና የተታገሉም ድምፅ ያሳሰሙበትን መሬ ከር ለመቀጋት «ግብሂስ» አድርገን ከኢ-ሕ-አፓ ጋር መጓዳኘት ያስኖቸው እነዚሁ ቁተራግጂች» እንደሆኑ ግልፅ ይሆንልናል። ለመሆኑ የኢ-ሕ-አፓ አቋም ምን ነበር ? ደርግ ለጭቁኖች ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ሬዶም ሊጸ ትድ አይችልም። ዲሞክራሲ ከሥል ጣን ተነስቱ የሚቀርብ ጥያቄ አይደ ለም። ስለዚህም ከደርግ ዲሞክራሲ ያዊ መብቶችን መጠበቅ የማሕነት ነው። ይልቁንስ ደርግ እንዲወድቅና በኀዲያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲ ተካ መታገል አለብን ብለው ነበር። ታዲያ እነዚህስ ተራግጂች ፣ በደርግ ጥያቄ በቅርፅና በመልክ ከልሆነ በስተቀር በይዘት ከኢህአፓ ምን ያህል ይለዩ ይሆን ? ኢ-ሕ-አፓ በዘው ምክንያት ሥልጣን ስመረከብ የጅመውን ያህል እነዘህ ደግሞ በሥልጣን አካ ባቢ ተሰጥፈው ለመቆየት ሲሉ ይህ ንኑ ምክንያት ገጸበረከት አቅርበዋል። ባጭሩ እነዘህ «ተራግጂች» አድር ባይነት የሚያዋጣ መስሏቸው ለዲሞ ክራሲያዊ መብቶች የሚሥረገውን ትግል ለመከላከል ሲሉ የሰፈው ሕዝብ ወገን ነው ከሚሉት መንግሥት፣ ይህ መብት በእስቸኳይ እንደሚለቀቅ ለሕ ዝብ ቃል ከገባ መንግሥት ዲሞክራሲ ልዩነኛም ይሉናል። ስፈው ሕዝብ የመንግሥት ሥልጣን ከመጨበጡ በፊት ይሆን መብት ስለማይኮነፍ ፈቀቅርቡ ትጉናጸፉለህ ተቡ። ቃል ተገብቶልኛልህ ብሎ መውናበድ የለ በትም ማለታቸው እንደሆነ ግልፅ ነው። እንግዲህ እነኚህ «ተራግጂች» ታሪክ የኢ.ሕ.አፓን አቋም መለሶ ትክ ክል አድርገውታል ብለው ሊያሳዎጉን ካሉተነሡ በስተቀር ፤ ከእብሮቱ ተገኝ ራትው በሥልጣን አካባቢ ጥገኝነት እንዲሰጣቸው ሲሉ የሚሰብዳት እነ ርሱ እንጂ ሐቀኛ ተራግጂች አይደ ሉም እንላለን።

፪- ሐቀኛ ተራግጂች ሰፈው ሕዝብ ነቅቷል ተደራጅቷል ፣ ታጥቋል፣ የመ ንግሥት ሥልጣን አሠን ሊደርስበ ይች ላል የሚል እሳቦ የላቸውም። ገን ግን እነኚህ አድርባዮችና አጨናቀጮች ዲሞክራሲ በትክል እንደሚተኛ የደረ ሰበት ዛፉ ገና እንዳልሠነ አናውቃ ለን። በእነርሱ ዪት ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሲሞቁናኝ ያለገደብ የሚ ሰው የትግል ሳይሆነ የልመና መሬ ክር ሆነብን ብለው መወርወራቸው ይሆን ?

ክፍ ብለን እንደመቀስነው እነዚህ ተራግጂች» ሰፈው ሕዝብ ጊዜያዊ ወታራዊውን መንግሥት «ጥየኛ ከሆዜያ ክፍት በላይ ሃግታል እስ ከአሁንም ድረስ የዘነየው በደርግ በነበ ቱት አጋዳሪ የውስጥ አርጅቸች ሚራ ነው ተብለናል። ዲሞክራሲያዊ መብ ቶችን ለጭቁኖች ያለገደብ የሚያደር ነውጥጅ አሠኑት ይለቀቅልን» ብሎ እንዲያዘኮግር የመሰዴት አቋም ነው። ይህ «ግራ» መሰል አደር ባይና ተልማ ጣጭአቋም በራሱ «ሰፈው ሕዝብ ሆይ ዲሞክራሲን ከደርግ እጣገለጭ ብለህ አትመናበድ ይልቁንስ በትግል ሥል ጣን በትውጠጥ ብቻ ነው የምታገ ኘው በማለት የአሕአፓን አቋም መልሶ የሚያስተጋባ እንጂ ሌላ ምክ ተኛአቋም ይሆን የሚችል አይደለም። ይህም በዘርፍ ዲሞክራሲ እንዲታገን አያተባበሉ ፣ በግልፅ ደግሞ ለሰፈው ሕዝብ ግራ እጂ እያሩነው በአድርባይ ነት ለመኖር ሲባል የሚዘረር የተ ልባሽኛ አቋም ነው።

መቸም በታሪክ ፣ «ቀልብሳቦች የተ ሰሳ መልክ እየሰኩ መሞከራቸው የታወቀ ነው። የተኛና «ግራ» አደር ባዮች የኢትዮጵያም አብዮት ማን እስከመታ ድረስ ከዚያም በኋላ ሰፈ ጀም ጊዜ ተመልሰው መሞጣታቸው አይቀርም። ከዘህም ተልባሽ ለመ ሆን የተጅ የኢሕአፓን ቀሚስ መዋበ እያስለገሙም ፣ ቀልባሽ የፓለቲካ መሥመርን ከመስተ ቃትር ከአዩፀረ ኢሕአፓን ካባ ደብሰ አብቅቱን መዋ ጋት እንደሚችል የጨም አገር ልዝ ቦች አብቶት መልሰ ግረጋገጭ የማይ ቀር ይመስለል።

ሐቀኛ ተራግጂች ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ እሁኑት እንዲለቀቁ ትግሉን ይቀጥላሉ። የዘህ መብት እሁኑት መለቀቅ የማይበገግ ቸው ተራግጂችና በገኢ አደግሞ ወን በሥነቃወቁ እንጂ በእርጋታ ቃሎች ጥያቄውን ለመጨመድ መሞክ ራቸው ወቱ እደር ከመጋለጥ አያድ ናቸውም። ያለው ሁለት አማን ሁለት መሥመር ብቻ ነው። አደናጋሪዎች ተስማሚዎችና አደርባዮች በሥል ጣን አነሳሳቢ ዕድማያቸውን ለማራመም የሚያደርጉት መፍመርመር ብቻ ተኛ የሚባል አዲስ አብዮታዊ ሥፍራ አያስገኝላቸውም። ሰፈው ሕዝብና አያስገኝላቸውም። ሰፈው ሕዝብና ለአብዮቱ የቆሙ ሐቀኛ ወገኖች የተል ባሹችን የተንሠል ዘዴዎች ይነቱቁም ዋል ፤ ያክቨሏቸዋል።

ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ እሁኑት !

ለመናባኛች ይጋለጣሉ

ድሉ የሰፈው ሕዝብ ነው።

አዲስ ዘመን ጋዜጣ ፮ ቀን ፲፱፻፸ ዓመተ ምሕረት።

ሰ ሰ ዲ ሞ ክ ራ ሲ

— ዘመን ያርነት

ይህ ጽሑፍ ከተቅምት ፭/፸፱ ዓም ጀምር ለ፫ ቀናት ዘልዲስ ዘመን አብ ዮታዊ መድረክ ሳም ያዘ ሥር ብጸለጥ ከፉሲ መብቶች መጨቀት እንዳንደ ግ ምቶች» ዘርሷል ርእስ ለውይይት ቡት ከታታይ ለቀረበው አስተያየት የተሰጠ ሂሳዊ ምላሽ ነው። የተጻፈውም ፍሬ ድሬስ ኢንግለስ ነው። ከአእርስ በርስ መወቃቀስ ከሰሂስ ... መግባባትም

ዘላቂ አድነትም ጭምር ሊኖር አይች ልም...» ብሎ የኮግለሪውን ምርኩዝና መሠረት በማድረግ ነው። በርግጥ ይህ ሂስ የሚመስከታቸው ግምት ለትፉሲ ምች ግንነት በጋዜጣው ላይ ከመጀመ ሪያውኑም ቢሆን እንደታየው ባጭ ነው። ስም የለሽ ነው። ይሁንና እነው ራሱ ለሂሱ አቀራረብ ያመኸን ዘንድ

ባጭሙን በታ ጭልቂ ለማግት አትቻ ቢያኖር ሳገግኙ» የሚል ጊዜያዊ መል ያ እንድጠቀም ተገድጂለሁ። ይህ መታወቂያችን አይደገም ወይም አይ ደለም ብለው ቅዋሚ ካሰሙም ወደፊት በፈለጉት ስም እንደጠራቸው ግንኙታ ችውን እንዲያስታውሱም አሳስባለሁ።

ግና ከዚህ በፊት ሚያዝያ ፳፱/፷፱ በሳሪ ዱቄ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ላይ «እነየማነ ቮርነት» ብለው እንደጻፉት ሰዎች በእንዳንድ ለው በኛ እንላይነሣዴና ትዝብትን እንዳያተርፉም እጠይቃ ለሁ ።

በተለያዩ ጊዜያቶችና በሌያሌ ሥፍ ራዎች ስለዲሞክራሲና ስለዲሞክራ ሲያዊ መብቶች በእስተጎሰብ የተለያዩ አጠቦታዊና አደንገሬ ምሁራን በርከት ያሉ ጽሑፎችንና የተለያዩ ዲሲኩሬሮችን እንደየአመቺነቱ ለየተከታዮቻቸው ዥውም የመደብ ጎብረተሰብ ውስጥ የትግል ውጤት ሆነው እንደሚገኙና በተቀነባበረ የሕዝብ ሐሳቦ ትግልም በእጥባቡ ሊክበሩ እንደሚችሉ ለማሳ የት ላይ ላዩን ጥረት ግድፈቻቸውም የሚታወስ ነው። ፉቱ ግን አብዛኞቻችሁ ምሁራን የዲሞክራሲ መብቶች ከየት መጥተው ወይም ተግኝተው በመልዳግ በሰመታ መልክ እንደሚቀርቡና ከየት ኖረው እንደሌሉ በሆን ሁኔታ ውስጥ እንደሚለቀቁ ወይም እንደሚፈቀሉ ወይም እንደሚከበሩ በሚነባ ዘርዝረው ለብዙኀኑ ጭቁን ሕዝብ ባለመግለጽ ቸው ይገኙ አሁንም የዲሞክራሲና የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ የእንዕት ልገ ጨዋታ ሆኖ እየቃየ ነው። የአሌስ ዘመን ጋዜጣ አዘጋጅም የቀያቂው ፍሣፊ አለማግኘት በላባሰበው ፍጥነት ለጥ ራት» በሚል መግለጫ ቀነሳለቆ ቀልማ ጀች መፍትሔ ይሆናል ብለው ያሰቡ ትን ሁሉ እንዲልክሉት እያጠየቀ ነው። በዚህም መሠረት ፩ነማኞቹ የው ይይት ጽሑፋቸውን ለዘመን ጋዜጣ ልከው ወጥተላቸዋል። እኔም ይህን መልዕክለሁ። በቅድሚያ ወደጅሔሬ ቁራንር ከመሀለቆ በፊት ግን ዲሞክራ ሲና የዲሞክራሲመብቶችምንእንደሆኑ አቅርቢውና አሰፎተው እንደነበር የማ ስታወስ ነው። ከመጻሳቸው ከፊውሎም የዲሞክራሲ መብቶች ለሰቁኖች ያለ ገደብ እንደሰጠ በጥደጋጋሚ መጠየቃ ችውና ሴሎችም እንደየሁኔው እንዲ ለተቋሳቸው ወይም እንዲፈቅዳሳቸው ሚባሰባቸው እንዲሁም አንዳንዶች የዲሞክራሲን የመደብ ዕገሰ ሴሳብነት በመረዳት የዲሞክራሲ መብቶች ይጠን በጎብረተሰብ የእድገት ታሪክ ውስጥ መጪ ለምንና በማን እንደተጣኙ መቼስ እንዳልነበሩና እንደማይኖሩ መግ ለጹ ለውይይቱ መንገድ የሚከፍትና የሚጠቅም መሰሎ ከለታየን እርገዋለ ሁና እንባቢ በየምሮና እንዲከታተለው እጠይቃለሁ ።

የሰው በሰው መበዝበዝና መጨቆን ባልነበረበትና የሰው ልጅ ዘርም ተነ ፊፊ ለሰዎችና ፍላጎትባላቸው የተለያዩ ወገኖች ተከፋፍሎ እርስ በርሱ ሊታገል ባልታየበትበጥንታዊው የጋር የጌ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ዲሞክራሲ የሚለው ዕገሰ ሐሳብ የሚታወቅ ለል ነበረም። የዲሞክራሲ ታሪካዊ አመጣ ጥና አስተዳደግ ከመደቦች አፈጣጠ ርና አጠቃላይ ሁኔታ ጋር መሠረታዊና ዘላቂ ግንኙነት የነበረው ያለውና የሚ ዋረው ነው። ቢጋርዮሹ ጎብረተሰብ የማኅበራዊ ሕልውና ውሰተም ለተወ ስነ መጸባዊ ኅላማ ቀረጥ የሚያስቀር ዋና የተለየ ሕግ የሚያረት ከቡራንና ለዋቂ ሰዎች የተጠቆሙበት የተደ ራጀ የመንግሥት ኃይል አልነበረም።

አጨኖርም። በመሠረቱ ዲሞክ ራሲም የመንግሥት እንዳ መልክ እን ደመሆኑ መጠን በዚያ መንግሥት ይልለበት የነብረተሰብ የተወሰነ እድ ነት ደረጃ ላይ ያልነበረና ወደፊትም በከፍተኛው የመደብ አልባ ሥርዓተ ማኅበርም ውስጥ የማይኖር እንጂ በማ ንኛውም ጊዜና ሥፍራ በውሰም ዓይ ነት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ፍጹምና ዘለዓለማዊ አስፈላጊና ፍቹ ያለውሆኖ የሚገኝ አይደለም። አይሆንምም። በተ ንታዊው የጋርዮሽ ጎብረተሰብ ውስጥ ቀነኛው ኃይል መላው ሕዝብ ነበር። በጎብረተሰቡ ውስጥ ያሉት አባሎች በሙሉ በመኻላቸው የነበረውን ማኅ በራዊ ግንኙነት ይቆጣጠሩ የነበሩት ባዘልማድ ኃይል ባገኙት ባህላዊ ዘይቤ ነበር። ይሁንና በዚያን መደብ አልባ ጎብረተሰብ ውስጥ ያቆጠቆጠው የሥራ ክፍፍል ከእዲስ የሥርት ግንኙ ነትና ልውውጥ ጋር እየተስፋፋ መታ የት ሲጀምርና ለመደቦችም ታሪካዊ አመጣጥ መሠረቱን እያስግግ እያ ጠነከረ ሲሳዝ ያ ዋንታቂው የኩግ ባህላዊ አስተሳሰደ በእድገት ሂደት ላይ ያለውን አዲስ የግንኙነት ሥርዓት በቁጥተቱ ሥር ለማዋል ባለመቻሉ የጎድ ዩታውን ከሱ ለየትና ጠንከር ብሎ ለተደራጀው አዲስ ኃይል መል ቀቅ ታሪካዊው ግዴታ ሆኖ ተገኘ።

በጎብረተሰቡ የኢኮኖሚ መዋቅርም የበላይነትን የተቀዳጀው ወገንም ይህን በዓይነቱ፣ በይዘቱና በኀላማው አዲስ የሆነውንና መለውን የጎብረተሰብ አባል የማይመክለውን የመጨቆኛና የመቆጣጠሪያ ኃይል ከአዲስ አስቱሳ ሰብና መሪ እምነት ጋር አከለው እንደ ግደራጀትና የመገከከብ ታሪካዊ ኃላፊነት ወደቀበት። ይህ በተወሰነ የጎ ብረተሰብ የእድገት ደረጃ ላይ የማይ ጣጣው የመደቦች ቅራኔ ነውጨቋኙና መሣሪያ ሆኖ የተገኘው አዲስኃይል(የ መንግሥት ሥም) የምርት መሳሳያዎ ችን በጠቃል ባለቤትነት ለያዘው ወገን እንደመጨቆኚያናንእንደመበዝበዣና ዓይ ነትኖ መሣሪያ ሆኖ ከማገልገሉም በላይ፣ባላቸውና በሌላቸው እንዲሁም በሌላቸውና በሌላቸው ባላቸውና ባላ ቸው መኻል የነበረውን ያለውን ማኅ በራዊና ኢኮኖሚያው ግንኙነቶችን በመቆጣጠር የመጥቃ አስከባሪነቱን ፣ የሕግ አርቃቂነቱን ወዘተ ሥራ ማከና ወኑን ቀጠለ። ይህን አዲስ ኃይል እን ከባከበው ያደራጁት በኢኮኖሚው መዋቅር ዋና የበላይነትን ዕቃ የተቁ ጻጁት ሁሰቃሎች ነበሩና የሚያዙትም በጥቅማቸው እንጎር የሚያንቀላቅሱ ትም እነሱው ነበሩ። ስለሆነም አዛ ዦች ዋቹዎቹ ነጥቦች መሆን አልተሳ ናሞውም። እነዚህም አዛዦች የኢኮ ኖሚና የፖለቲክ የበላይነታቸውን ለማጠናከርና ተቀናቃኞቻቸውን ለማ ሳከም የተጠቀሙበትን የዚህን አዲስ ኃይል አስፈላጊነትና ለዘለዓለማዊነት በመሰበክ ጭቁኖች ሁሉ እንዲታዘዙ ለበኩ። የነሱን አስተሳሰብ የጎብረተ ሰቡ መሪና ገዥ አስተሳሰብ ሆነ። በገ ዢዎቹ አስተሳሰብም በመመራት ጭቁ ኖች ለቅመሰነም ታሪካዊ ጊዜ አነበ ሩት። በሕብረተሰብ ውስጥ ያለውን ቅጥር ጣቂ ነጭካኔ ነተንኮል ብዝበዛ ልዩዉጣም ሁሉን ወደትክክለኛ ጉዳና

የሚመራ ዘለዓለማዊ ኃይል ሰለመሰላ ቸው ታዘዙት። በውክልና የቆመውና የሚያስከብረው የመላውን ጎብረተሰብ ጥቅም ሰለምኖ ያጥቃ ነው ብለው ሰላ ሰቡም ደንቅት። የኃላ ኃላ ግን ከየቀኑ ተግባራዊ የኑሮ ግንኙነቶቻቸው እው ቀትን እየቀሰሙና ተጨባጭን ነባራዊ ሁኔታእየተረዱ ሲመጡየገዥውመደብ አባላት ስለሌሏቸ መንግሥታዊ ኃይል ተግባር የነገሮቹው ሁሉ እውነት አለ መሆኑን ግወቅ ጀግመሩ። አዲሱ መንግሥታዊ ኃይል የነሱን ብሶትና ችግር ከማባባስ ይልቅ እንደማያቃ ለልና በምቅሱም የገዥውን መደብ አባላት ጥቅም ሰለም በመገከባበብ ለነሱ የሚያሣዝ የነሱ መጨቆኝያ መሣሪያም እንደሆን ተገነዘቡ። በዚህ ኃይል ፊት ሁሉም በእኩልነት እንደማይታዩ፤ እንደማይጠበቁ፤ እን ደማይጠቀሙና እንደማይጨቆኑም ተረዱ። ይህ ኃይል ለተወሰኑ የገዥው መደብ አባላት የመወያየትነየመሰብ በዘሁታቃውሞን የማሰማት፤ የመደራ ጀት ወዘተ መብታቸውንና በውስ ጡም የመሳተፍ ግዴታቸውን በሕግ እንደሚያስከብርና ለተወሰኑ የተገ ዥው ወገኖች ግን የተጠቀሱትን መብ ቶች ጥሰ በሥርዓት ሰም እንደሚሣሣ ናቸውም እውቁ። ስለሆነም እንደየ ሁኔታው ይህን ኃይል የአለመታዘዝና የአለማክበር ስሜትና ሌላ አዲስ ኃይል የማቋቋም ፍላጎታቸውም እየጸበረ ሔደ።

በመሠረቱ ዲሞክራሲ ለመጀመሪያ ጊዜ በራሱ በቃሉ እንኳ የታውቀው ከላይ የተጠቀሰው አዲስ መንግሥ ታዊ ኃይል አደልም ሥራውን አፋ ፍሞ ያከሌድ በነበረበት ታሪካዊ ወቅትና የጭቁኖችም ጭጣኖች የትግል እያየለ በሔደበት ሁኔታ ውስጥ ነበር። ቃሉም እንዳለ የተመረሰው «ሕዝባዊ» ና «አገዛዝ» የሚለውን ትርጉም ካዘ ሉት ሁለት የግሪክ ቃላት ነበር። ሰመ ጀመሪያ ጊዜ በታሪክ ገጽ ላይ የታየ ውም ተፃራሪ ኅላማና ፍላጎት ያላቸው መደቦች በከፍተኛ ትግል ተወጥረው «ሕዝብ» የሚለው ቃል ለተለያዩ መደቦች የተለያየ ትርጉም መስጠት የጀመረበት ወቅት ነበር። ለምሳሌ በባርያ አንዳረው ጎብረተሰብ ውስጥ «ሕዝብ» የሚለው ቃል ባርቹን የሚ ያጠቃልል አልነበረም።

በፊውዳሉም ሥርዓት ማኅበር ውስጥ የተኛው መደብ አባላት ራሳቸ ውን እንደሕዝብና ተወካይ ሲቆጥሩ የተገዣውን መደብ አባላት ግን የአገ ሪቱም ዜጐች እንዳልሆኑ አድርገው ይገምቱ ነበር። በኮፐታሊስቱ ጎብረተ ሰብ ውስጥም ምንም እንኳ መላው ሕዝብ በሕግ ፊት እኩል ነው ተብሎ ቢታወጅም ሕዝባዊ የሚለው ቃል በሕት የሚያስማሳው የምርት መገል ገያዎችን በማል ንብረትነት አከብ ተው ለያዙት ወገኖች ብቻ ነው። አለ ተብሎ የሚመሀለትም «ሕዝባዊ መንግሥት» የነዚሁ ጥቂት ካፒታሊ ስቶች ጥቅም ነክከከበረያና የጭቁኑን ወገአደር ኃያላዊ እንቅስቃሴ ግዳክ ሚያ መጨቆኛ መሣሪያ ነበር።ነው ም። በዚሁም አኳያ ጭቁኖች በማንባር ቀደሙ ማለ ፓርቲያቸው መሪነት የመንግሥት ሥልጣንን በጨበጡ በት አገርም ውስጥ «ሕዝባዊ» የሚለው ቃል የሚገልጸው በአጨኖሚር መዋ ቅር ያን የበላይነቱን ሥፍራ የያዙትን ጭቁኖች ነው። መንግሥቱም የሚያ ገለግለው ሰጭቁኖች ነው። በሌላ ጥቂ ቶች ሰብዙኀን ውሳኔ የተገዙበትም «ሕዝባዊ ሥርዓት» ይኸ ነው።

በሽርንጥ ዲሞክራሲ የሚለው ጽንሰ ሀሳብ በታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከታየበት ዕለት ጀምር ይኸው እስከ አሁን ድረስ በተያያዩ ሁኔታ የጭቁኖ ችን ስሜት እንደተስቀሰና የጨቋኞ ችን ምኞት እንደአሸበረ እንደእስጨ ነቀ ነው። ለጨቋኞችና ለጭቁን ኃይላት የቆሙ የተለያዩ ምሁራንንም በተከከ ለኛ አተረጓጐሙና አሠራሩ ጉዳይ እንደእስራኤር እንደአጋደለና እንዳኮ ራረፈ ነው። አም ! በእያሌ ሥፍራዎ ችና በተለያዩ ጊዜያቶች በመደቦች መኻል ያለውንና የሚኖረውን ኢኮኖ ሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት ጠንቅ ቀው ያልተረዱና የመንግሥትን መለ አባይ ይዘት ዓላማ ፣ መርምረው ያለ ወቅ በርከታ የከበርቱ ጸሐፊያን ዲሞ ክራሲን በተሬ ትርጉሙ እየመሰጹ እያታለሱበት ነው። በመደብ ጎብረ ተሰብ ውስጥ የሚታየውን ግፍ ጭካኔ ብዝበዛ እደልእ ወዘተ የሚያጠፋውና በመደቦች መኻል ያለውን ልዩነት ቅራኔ ትግል እስከነ አካቴው የሚያስ ወግደው ዲሞክራሲ» ስለሆነ ፣ በሰ ዎች መኻል እንድነትን የሚፈጥርና የሰዎችን ፍላጐት ለዘለቂታው የሚያ ረክው ዲሞክራሲ ስለሆነ የሰውን ልጅ ሰብእና መብት ነፃነትእኩልነትየሚ ያስከብርና አገሮችን ከእርስ በርስ ጦር ነት የሚያድን ዲሞክራሲ ስለሆነ ፣ ለዲሞክራሲ መታገል እብዮታዊነት ነው በማለት ብዙዎችን ጭቁኖች ልት ግልለመጊያ እየቀሰቀሱቡትና እያዘጋ ጁበት ነው። በሳርያውና በፊውዳሉ ሥርዓት ግህበርም ውስጥ ዲሞክራሲ በፍጹም እንደሌለ በመስበክ ጭቁኖ ችን በዲሞክራሲ ቀለ ሥር ክልለው በራሳቸው መሪነት ከዚህ በፊት እንዳ ደረጉት የራሳቸውን «ዲሞክራሲ» ወይም «ሕዝባዊ አገዛዝ» በየቦታው ለመመሥረት እየታገሉ ነው። ሐቁ ግን በነሱ «ሕዝባዊ»በተባለው አገዛዝ ውስጥ ጭቁኖች ከሥታይ ፣ ከረቃብ ፣ ከሥራ እጦትና ከእርዛት በስተቀር ምንም የሚያስተማምን እኩልነትና ነፃነት እንዳላገኙ እንደማያገኙ ግልጽ እየሆነ መጨዱ ነው። ሊኑንም ስለነሱ ምንነትና ስለሥርዓታቸውም ሲናገር «— ችግርና ፍላጐት ምን እንደሆነ ስማያውቅና ከጭቁኖች ጋር የቅርብ ግንኙነት መሥርቶ የነሱን መከራ ላልተረዳ ሰው ፣ በካፒታሊስቱ ጎብረ ተሰብ ውስጥ ቦጭቁኖች ላይ የሚደረ ጀሩት ገደቦችና ልዩ ልዩ መሰናክሎች ቀላል መስለው ይታዩት ይሆናል። ሐቁ ግን እንዘህዘልዩ ልዩ ገደቦችና መሰናክሎች ጭቁኖች በዚያ በሚለፈፍ ለት «ሕዝባዊ አገዛዝ» ውስጥ እንዳይ ሳተፉ በመጭመቅ ወደውጪ የሚያ ገልሏቸው መሆኑ ነው—» ብሎ ነበር።

በመሠረቱ ማርክሲስቶች «ሕዝብ» የሚለው ቃል ለተለያዩ መደቦች የሚ ስጠውን የተለያየ ትርጉም ለክርክራ ችው ምሰሶ በማድረግ ይኸው መደ ቦች ከተፈጠሩበት ታሪካዊ ወቅት ጀምሮ ወደፊት እስከሚጠፋበት የተ መሰነ ወቅት ድረስ በነበሩትና በሚኖ

ሩት ሥርዓቶች ውስጥ ሁሉ ዲሞክራሲ ከመንግሥት የተለያዩ መልኮች እንደ አንድ ሆኖ የንበረና ዘንገኛውም ጊዜ ከሌላኛው የመንግሥት ገጽታ ከበላይ ጎዥነት ተነጥሎ የማይመረመርና የማይታይ ያልታየ አንደሆነ በሳይንሣዊ መንገድ በማስረዳት ከላይ የተገለጹት የከበርቴ ምሁራን የአፉትን ሁሉ ውድቅ ማድረጋቸው ገሃድ ወጥቷል። እየወጣም ነው። በአንዳንዱም ማንኛውም መንግሥት በአንድ ጊዜ በጥብረቱበት የኢኮኖሚ መዋቅር ዋና የበላይነትን በታ ሊያሰፉት የገዥ መደብ አባሎች የመናገር የመወያየት የመወቃቀስ የመቧቀስ ወይተ መብታቸውን በሕግ የሚያስከብርና እነሱም ባለሥራቱ ይህንኑ አስጊነትም የተደቀደ የሚደ ቅድ አልነበረም ማለት ነው። ይህ ደግሞ ሊሆን የማይችል ሆኖ የማያ ውቅ ነገር ነውና ዘንግኦችም ቃረመ አም በሥርዓቱ ውስጥ የነገርውን መደብ አባላት የዲሞክራሲ መብቶች በፋትና ቱበት የሚወስነውም እንዚሁ አባላት በጉብረተሰቡ ውስጥ ከሱት የተወሰኑ የምርት መገልገያዎች (መሣሪያዎች) ጋር ያላቸው የህብት (የምርት) ግንኙ ነት ነው ማለትም መንግሥት የላዕላት መዋቅሩ (እስተላሰሰችን፤ እምነቶችን ልዩ ልዩ ተቋሞችን ድርጅቶችን ርዕ ዮት ዓለማዊ ግንኙነቶችን ዋቀር ያጠቃልላል) አንዱ አካል ስለሆነና ዲሞክራሲም የመንግሥት አንዱ ገጽታ በመሆኑ የሚወሰነው በጉብረተ ሰቡ ውስጥ በተወሰነ ታሳሪዊ ወቅት በሚኖረው የተወሰነ የምርት ግንኙ ነት ነው ማለት ነው። ተግባባን ?

ፀሁሲኖና ደረጀ እናንተ ገማቾቼ የመንግሥት ተግባር (ሥራ) የጭቁ ኖችን እንትስታሬና ጥንካሬ ማዳከምና ማፈን ብቻ ሳይሆን የነገሥው መደብ አባላት ኃይል ደጠንከር ዘንድም በገ ዥው መደብ አባላት መሐል የሚኖረ ውን ግንኙነትም ዓይነት ግንኙነት የመቆጣጠርም ጭምር አንዳደሆነ ትረዱ ዘንድ እጠይቃለሁ። ይህ የመ ንግሥት ተግባር ደዛሞ በከርያውም ሆነ በክርታሲስቱ ዓለም ያለ የነበር አንዚ እናንተ እንደምትሉት በፈው ዳሉ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ብቻ የታተ አይደለም። ዲሞክራሲና እምነትንን ትም የአንድ መንግሥት ሁሉት መል ኮች ሆነው መተያታቸው ብጥርያው ፣ በፈውዳሉና በከርታሲስቱ ዓለምየታየ ነው። ይህን ከተቃወማችሁ ማርከስ ለስርርጀው ኤኮኖሚስቶች ሁሉት ዓይ ነት ድርጅታዊ ተቋሞች አሉ (አርቲ ፊሻልና ተፈጥሮአዊ) ለነሱ በፈውዳሉ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ያሉት ፈውዳ ላዊ መንግሥት በጉብረተሰቡ ውስጥ ላሱት ተቋሞች አርቴፈሻል ሲሆን ነበክፕ ታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ያሉ ት ግን ተፈጥሮአዊ ተቋሞች ናቸው። በዚህም ማዎታቸው እነዚያን ሁለት ዓይነት የይማኅቱትን የሚመሠርቱ ትንና የራሳቸው ያልሆነውን ሁሉ እን ደሰው ሠራሽ የራሳቸውን ግን ከእግ ዜር እንደመጣ እድርገው የሚሰብኩ ቱን ሃይማኖቶች ይመስላሉ፣ . . ብሎ የጸፈውን ልብ በላችሁ ታቱት ዘንድ ጠቅሼለሁ ፫

ከዚያም የመንግሥት መሳ ጠባይ አቋምና በመደቦች መሐል ያለውን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነቶች ጠንቅቃችሁ ባለመረዳታችሁ . . . የፈ ውዳሉን ላዕላዊ መዋቅር ዓይነተኛ ከሚያደርጉት ባሕሪዎች አንዱ የዲ ሞክራሲ አለመኖር ብቻ ሳይሆን፤ ፖለ ቲካ የጥቂት ባለመፈቶች ጭኖፖሊ መሆኗም ጭምር ነው . . . ለሰፈው ሕዝብ የፖለቲካ ዓለም የሚባል ነገር የለም ብላችሁ ያሠፈራችሁት አስተያ የት በለፖለቲካና ስለዲሞክራሲ ያላ ችሁን እምነት ገልጸታል። በእርግጥ በጉብረተሰቡ የኢኮኖሚ መዋቅር ዋና የበላይነቱን የያዘው መነን የፖለቲካ የበላይነቱንም መቆጣጀቱ በሁሉም የመደብ ሥርዓት ማኅበር ውስጥ የሚ ታይ የታየ ሐቅ እንጂ እናንተ ገማቾቼ እንዳሰባችሁት በፈውዳሉ ሥርዓተ ማኅበር የተገለጸው ልዩ ባሕርይ አል ነበረም። ፖለቲካም ማለት በጉብረተ ሰቡ የተወሰነ የኢኮኖሚ ኑሮም እን ዥር በተገፈራ መደቦች መሐል ያለውን መላ ግንኙነትና እነዚህም ተፃራሪ መደቦች የየራሳቸውን መደባዊ ዓላማ ከገቡ ለማድረስ የሚነገለገሉበትንየመ ንግሥት ሥልጣን ለመጨበጥ ወይም ለመሰባበር በመሐላቸው የሚያካሒዱ ትን መራርና ረዥም ትግል ተንትኖ የሚያሳውቅ ሰሚል ሳጀንሱ እንደሆን የተረዳችሁ አልመሰከሳም ፥ ስለዚህም እናንት ገማቾቹ እንሳሰባችሁት የፖለ ቲካው ዓለም የንዥው መደብ ዓለም ብቻ አይደለም ፤ የሚያጠቃልለውም በጉብረተሰቡ የተመሰነ የአድኅተ ደረጃ ውስጥ ያሉትን የንዥውን መደብ ድር ጅቶችንና አስተሳሰቦቹን ብቻ ሳይሆን፤ አጠቃላይ የፖለቲካ ተጻዋሮችን ማንኑ ነቶችን አስተሳሰቦችን ተማባሮችን ጭምር ነው። በዚህም መሠረት የተገ ዥው መደብ በንዥው መደብ አባሎች የፖለቲካ የበላይነት ላይ ሶሚኮሌ ደው ውጊያ ትጀጂ የነገ የፖለቲካው ዓለም አካል የሚሆን ነው። በፖለቲ ካው ዓለም ውስጥ ያሉት ሁለት ትላ ልቅ ኃይሎችም የንዥው መደብ የተ ደራጀው መንግሥታዊ ኃይልና ያልተ ደራጀው የብዙኃን ኃይል ናቸው። ከሁሉም ዋናው የንዥ መደብ መን ግሥታዊ ተቋም ነው የመደብ ትግ ልን ፖለቲካዊ ፈሳጽ መገንጋት ም ስሠት ነው። እርግጥ ፖለቲ ካዊ ግንኙነቶች የሚመሠረቱት አሁን እንደሚታየው በፖለቲካ ፓርቲዎችና ፖለቲከኞች ዓለማና ሐሳብ ቢሆንም እንኳ በፈውዳሉ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ዋቅቡን ሕዝብ ለተወሰነ ዓላማ አሰልፈው ልነነነት ይታገሉ የነበሩ ድብቅና ጎልጽ የነጽግኖት ሰዎችና ድርጅቶች ከፖለቲካው ጎሰም ተባቶ ቸች ነበሩ። ስለሆነም ሲሰፈው ሕዝብ የፖለቲካ ዓለም የሚባል ነገር የለም የሚለው አነጋገራችሁ ወይም አንግ መታችሁ ተቀባይነት የሉለው ነው፤ ኢግርከሳሚ ነው።

ከዚያም በጽሑፋችሁ ውስጥ ዛየዲ ሞክራቲክ አብዮት በላዕላዊ መዋቅሩ ደረሻ ሰፊውን ሕዝብ ፖለቲካ ልሌባ የሚያደርገውንና መብቶቹን የሚነፍ ገውን ሥርዓት ለመደምሰስ ሲል የሰ ውን ልጅ እኩልነት የሚያዘሥሩ መሠ ክርችን ያከተጋባል ፤ ለደሙ ሕዝብ በፖለቲካ እንዲሳተፍ በር ይክፍትለ ታል..... በግሰት ያሠፈራችሁት ዋርዣው ያኒ የአሁኑ ጀባውን ከመያዙ በፊት ለስሁ አለሁ ባጅ ሆኖ በዲሞክ ራሲ ስም ዋቁናች የሱን የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት የሚያበሥረውን ሥርዓት ባለማወላወል ታቅለው እንዲ ያስገኙ የሚያበረታታበት የሚሰብኩት ነበር እንጂ ማርከሰሚ ትንታኔ አይደ ለም። ከዚያም ለኋንን በማስረጃነት ጠርታችሁ «ኢምፔርያሊዝም በመ ሠረቱ ፀረ ዲሞክራሲ ነው። በጠቅላ ላው መሥመሩ ለደኃሪነትን የሚያን ፀባርቅ ከስተት ነው» ብሎችኋል። ይህ ን ማቅረባችሁ ጥሩ ነው። የሚያሳዝ ነው ግን ማርከስ ሌኒን እንደገለጹት ማንኛውም ከስተት የተቃራኒዎች ው ሕደት መሆንን አለመረዳታችሁ ነው። እንድን ከስተት በትክክል ለመረዳት ይህ ከሌሎቹ ከስተቶች ጋር ያለውን ግንኙነት አመጣጡን አካሔዱንከብዙ አቅጣጫ መርምራችሁ ለማወቅ ግዴታ እንደተጣለባችሁ አለመገንዘባችሁ ነው። በእሱ በዘመን ኢምፔሪያሊ ዝም ሁለት ተገራሪ ኀምሶች በመሐላ ቸው መራር ትግል እንደሚያካሔዱ ብታውቁም ከሁለቱ እንደኛው ለማ ሸነፍ በቅድሚያ ምን ምን ሃኅጅት ማሟላት እንዳለበት ለማወቅ አለመሞ ከራችሁ ነው።መሻሻል እድገት ለወጣ አንድነት የተቃራኒዎች ትግል ውጤት ሆነው ሊገኙንደሚችሉ መዘንጋታች ሁነው።ዲሞክራሲያመደብተግለኝላጭ ንቅተኛ ሰራ ለማድረግ የሚያስገል ያነለገል የመደብ ጽንሰ ሐሳብ መቃሚ መሣሪያ መሆኑን በቅጡ አለመመርመ ራችሁ ነው። ዲሞክራሲ በሽዕኑነቱበዓ ላማውና በይዘቱ በተለያዩ ሥርዓተ ማኅበራት ውስጥ አንድ አስመሆኑንና የተለያዩ መደቦች ግንኙቶምን ሁሉ ላይ ይህ እንደሚጎኛ መሠጻችሁ ነው።

ለናንተ የቡርጂዋ ዲሞክራሲ የፈ ጠረ ዲሞክራሲ የመነ አዲሩ ዲሞክ ራሲ ትርጉም አልባ ናቸው። ስለሆ ነም በጽሑፋችሁ ውስጥ የሞትፈ ጉት የዲሞክራሲ ዓይነት ቁን አንደ ሆን አልተገለጸም። ለናንተ የዲሞክ ራሲ መብቶች በጽሑፍ ሁሉን አበየ ረው ያለያሉ። ወላጅና ጠሳትን ያፋጥ ማሉ። ደንገጽር ያስያሉ። ተራማጅ ችን ያክትባብራሉ። ስለዚህም መለ ቀቃቸውን ወይቃችሁሉ። ይህንን ዋያቄያችሁን አሊቃወምም። ይሁ ንና እኔ የብዙኃኑ ሕዝብ እንቅስቃሴ ድል ይመታል ብዬ የምከራከረው ጭቁኑን ሕዝብ በትክክለኛው ሳይን ሳዊ ርዕዮተ ዓለም እንዚ ኢያንጸባያ ደራጅና ግዙታዊ እንቅስቃሴውን ወደ ነቃ የመደብ ትግል እቅጣጫ እየመሩ በጉብረተሰቡ ውስጥ ያለው ፖለቲካ ዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በትክክል በመተንተን ዋና ሚና የሚጫወቱትን መደቦች እየለዩ ችግሮችን እስከነመ ፍትሔያቸው በማቅረብ ጭቁን ሕዝብ ለጊዜያዊውና ለዘላቂው ድኩ በሚያካ ሔደው ትግል ማንባር ቀደም እየሆኑ የበራዎችን የአድኃሪዎችንና የፀረ አብዮት ኃይሎችን ሤራ ለማጋለጥና ለመደምሰስ ወደጓላቸው የማይሉ ሐቀኞ ተራማጆች በሌቀኖ ድርጅቶቻ ቸው አማካኝነት የመንግሥት ሥል ጣንን ከደጋፊዎቻቸው ጋር አስካፈጨ በጩ ደረስ የዲሞክራሲ መብቶች መለቀት እናንት የደረደራችሁትን ውሎ ሊያከኖ አይችልም በማለት ነው።

በመሠረቱ ሌኒንን በማስረጃነት በመጥቀስ በሶቪዬት ኅብረት በየካቲት ፲፱፻፲፯ የፈሞክራቲክ መብቶች ባይል ቀፁ ኖር የየቅዎችን አብዮት ማካሔድ እንደማይቻል ተናግራችኋል። አዚህ ላይ ብዙ መጻፍ ባልሻም እንኳ የጥቅ ምት አብዮት የተካሔደው ከየካቲት ጀምሮ ግማሽ ኃይል ያለው ደኅማ ጊዜ ያዊ አድኃሪ መንግሥት የዲሞክራቲክ መብቶችን በሕቅ ስለሰጠ ወይም ስላ ስከበረ ሳይሆን ፣ በተቃራኒው አንፃር የሕዝብ ኃይልና መብት ለማክበርና ለመቀበል ባለመፈለጉ እንዲሁም በዚ ያን ጊዜ በአገሪቱ ውስጥ የነበረው ተጨባጭ አብዮታዊ ሁኔታ ከሰዎች ተግባራዊ ንቃታዊ ድርጅት (ከቦልሼቪክ ከፓርቲ) ጋር ተሟልቶ የዚያን አብዮት ማካሔድ የገድ በመጠየቁ እንደነበር እረጋግጣለሁ ፡

ከጽሑፋችሁም ውስጥ «የዲሞክራቲክ መብቶች ባለመለቀቃቸው ብተ ራማጅ ድርጅቶችና በሕዝብ መ ሻል ያለው ግንኙነት የተዛባ ነው ... ቅዝ ባዊ ድርጅቶች ዲሞክራሲያዊ አሠራ ርን እንዲመከተላቸው መጠን በውስ

ጣቸው በመሳ ጉዞል «ዲሞክራሲያ
አለ » ከነሱ ውጭ ግን ባለመለቀቃ
ቸው ቢርከራሲው እንዚህን ድርጅቶች
ይሚናሞቸል » ሕዝባዊ ድርጅቶች
ይህን ለመቋቋም አንድም መሣሪያ የለ
ችውም ... » ብላችኋል ተራማጅ ድር
ጅቶች እውነተኞውን ግርከሲዝም
ሌኒኒዝም መመሪያ በመከተል ትግል
ካካሔዱ በሞንም ዓይነት መንገድ ከሕ
ዝብ ጋር የተዛባ ግንኙነትን ሊመሠ
ርቱ አይቹም » ይህም ሥራችው አይ
ሆንም » በሕዝቦችና በነሱ መኻል
ያለው ግንኙነትና እንድነት የተበተ
ካከለ ሆኖ ዘላቂ ድልን የሚያጐናጽፋ
ችው በአንድ መንገድ ሲመራ ብቻ
እንደሆነ ያውቃሉ » ይህም መንገድ
የግርከሲዝም ሌኒኒዝም ሳይንሳዊ
ጕዳና ብቻ እንደሚሆነ ይረዳሉ»
ያለው ሁኔታ እያስፀረሚጋቸውም » ለትግል ፈቃደኞ አይጠይቁም ግር
ክስ « . . . ሰዎች በእውነተኛ መንገድ
ለመተባበር ወይም በመኻሳቸው ቋሚ
እንድነትን ለመመሥረት ብቁ ሆነው
ይገኙ ዘንድ የግድ የጋራ የሆነ ፍላጎት
እንዲኖራቸው ያሻል » ይህ ፍላጎት
ሁሉንም በጋራ የሚመለከት እንዲሆን
ከተረዳን ያለው የሁብት ግንኙነት
የግድ መወገድ ይኖርበታል. . .ይህንን
ለማድረግ ግን ብቸኛና ሳይንሳዊ ዘዴ
ያለው የመገ እደራመደብብቻ ነው...»
ባለው መሠረት ወገ አደራን ለዚህ
ታሪካዊ ግዴታ ለማብቃት የሱን ሐቀኛ
ቆራጥ ብዙን ታታሪ ፓርቲ ለማወና
ከር ይተራሉ » ይህ ተረታቸው በመገ
አደሩ የመደብ እንቅስቃሴ ውስጥ ተገ
ልመ ፍሬ የሚኖረው ከመጋኞች ፣ ከአ
ድር ባይ ዕቺያሌስቶች ፣ ከኢኮኖሚስ
ቶችና ከሥርዓት አልበኞች ፣ ከጀብ
ደኞች ጋር በሚያካሔዱት መሪር የር
ዕየተንለሞና የትጥቅ ትግል ነው »
በመገአደራና በገበሬው እንዲሁም
በሴሎች ዋቄን ያጎብረተሰብ ክፍሎች
መኻል ያለው እንድነትም ተጠናክር
ለድል ይበቃ ዘንድ የሚያደርገውም
እነዚሁ ሐቀኛ ተራማጆች በሚያጐኑት
አጋጣሚ እየተጠቀሙ በየዕታው የን
ውስ ከበርቴዎችን ርዕዮተ ዓለምና የከ
በርቴዎችን ስድ ሰብከት አፈር ለማ
ስጋዋ የሚያካሒዱት ቆራጥና የማያመ
ላውል ትግል ነው » በግብረተሰቡም
ውስጥ የመሪነቱን ቦታ እንዲቀዳጅ
የሚያረጋቸውም አውራው ነገር አዋቂ
ንቁ ታጋይነታቸው ፣ ቆራጥነታቸው
አብዮታዊ ዲስፕሊን እከባሪነታቸው
አስተዋይነታቸው ተስፋ ያለመቁ
ረጥ እባያቸው ትክክሥተኝነታቸውና
ይህ ሁሉ መለያቸው ለሚንቀባረቅበት
መንካራ ድርጅታቸው የሚያሳይት
እምነት አከብሮትና ፍቅር ወዘተ
ቁምር ነው » በተረፈ የቀበል የመ
ኢ.ሠ.ማና የሸይ ቤት ለዩ ኢምከራሲ
እንደሌል ለማወቅም ሞከሩ » በአር
ሞተ ጽሑፉን ከማጠቃለሉ በፊት እና
ንቱ ጉግቸቹ በአብዮቱ ደኃፊ በሆኑ
መደቡት መኻል ያለው ትራኒ ለማቻ
ቻል ወይም ለመፍታት ወይም ለማብ
ሳሳት የሚሞክራቲክ መብቶች መለ
ቀቅ በኃይል የሚያስፈልግ መሆኑን
ከመቀሳቸው በኋላ ለጊዘው የሚያስፈ
ፈልጉትን ወስናችሁ» የመገባር ፣ የመ
ጻፍ፣የመደራጀት ፣የመሰብሰብ ሰላማዊ
ሰልፍ የማድረግ ብቻ በትክ ሳታውቁ
ስሁትት ውስጥ እንደወደቃችሁ ልነግ
ራችሁ እፈልጋለሁ » ይህም ስሁተታ
ችሁ በማንኛውም ታሪክዊ ወቅት
እንዚህ የጠቀሳችኋቸው መብቶች እና
ንቱ ካልፈለጋችኋቸው መብቶች
ግለትም ከሥራ የማቆም ከመሥራ
ጥና ከመሳሰሉት መብቶች ተንጣጥ
ለው የማይታዩ መሆናቸውን እለመ
ረዳታችሁና ሁሉን ለብቻ ለብቻ ለመ
መልከት መቃጣታችሁ ነው » ለጊ
ቤው ይህ ሃስ አጠቃላይ እንጂ መጪ
ረኛው እንጓልሆነ እየጠቀስኩ የዛሬ
ውን በዚሁ እቀግለቅ »

አ ላ ጐ በ ድ ድ ም

—ከመገ አደር

በቃኝ እንግዲህ አምርራለሉ ፣
በጭቁኖች ደም እዝንእለሉ ፣
እሥማቸው ይወጋሻል ፣
አርማቸው ይጠራሻል ፣
ትግሉን ቀዋል ይልሻል »
አድኃሪው በየቦታው ቢያናፋ ፣
ቢርከራቱ ቁልቁላውን ቢነፋ ፣
ለዓላማዩ ቆሚእለሉ ሳልቆርጥ ተስፋ ፣
አብዮቱም እንዲነፋ »
አሻፈረኝ ለአብዮቱ ፣
አላስቀለጠለሰም እያለሉ በሕይወቱ »
ግርከሲዝምን ፣ ሌኒንዝምን ተምሬለሉ ፣
ሳንይሱንም መመሪያዩ አደርጌእለሉ ፣
ከራሴም ጋር እንዲዋሐድ አጥራለሉ ፣
ነቅቼ አነቃለሉ ፣
ተደራጅችም አደራጃለሉ ፣
ምድረ አድኃሪን ለመደምሰስ ወስኘእለሉ »
አልሰግደም አላጐበድድም ፣
አብዮቱን ነፃነቱን አልክደም ፣
በአድርባይነት የጭቁኖችን መብት አልሸጥም፣
እኔነቴን አለሙም »
ጭቁኑ ሕዝብ እጅ ለጅ ተያይዟል ፣
አናርኪስቱን ፣ ቢርከራሊን ፣ ቀኝ ከንቱን ፣
አድርባዩን ይደመስሳል »

ሥልጣን ፈላጊ አደንፋጮን ፣
የቀኝ ከንፍ ኪሐዲውን ፣
በጭቁን ላይ ያመጻውን ፣
የቢርከራሲ ተቀጥላ የሆነውን »
እመታለሁ እደመስሳለሁ ፣
የዓዶኙን ደም አበቀላለሁ ፣
ፀረ ሕዝቦች አናርኪስቶች ከየሥር ቤት ቢለቀቁም ፣
እያስደንግጠንም ዓዶች !!
ይብልጥ ታጋዮች ቆራጮች እንሆናለን ፣
ግንቆመን ቢርከራሲ በጣጥሰን እንተላለን »
ሰብአዊ መብታችንን እናስከብራለን ፣
ድሉ የኛ ነውና እናሸንፋለን »
ለዲሞክራሲ ብዙ ጊዜ ታግለሃል ፣
በአድርባዮች ቢኪስመሰዎች ታግደሃል ፣
ለትግልህ ለመብትህ እንቅፋት ሆነውሃል »
ታገላቸው ፣ አጋልጣቸው ፣
ዋንካፊሆን ፣ ከንድሆን አሳያቸው ፣
ላያጠፉህ ላያስጠፉህ ደምስላቸው »
ዲሞክራሲ ቢታፈገ ፣
መብቶችህ ቢጠቡም ፣
ነፃ ርምጃ ቢነፈገህም ፣
የጮ ኢ ሠ ግን ገፅ ሰምሃል ፣
ነፃ ርምጃ ወሰድ ተሰኘሃል ፣
አንተም ቃል ከሰን ጎበትሃል »
በትግባር ተርኑም ጥረውን ፣
መገዋር ደመስስ እናርኪስቱን ፣
የታጋይ ደም የጠጣውን ፣
የአድኃሪ ፣ የሲ· አይ· ኤ· የአድርባይ ደላለውን ፣
ስንቅ ተራግጮ የቀበለ ፣ የወሄደር ተመራቂ ፣
በየቦታው ለአብዮቱ ደመን ሊረጭ ፣
ፅረ ሕዝብ ኢ· ሕ· ኦ· ፓ· ሊዘል ሊፈነጭ ፣
ጭቁኑ ሕዝብ ቀኙቱ እያረረ ሊቀጭ »
ይሻላል እንየ. ማየቱ ?
ጭቁን ሲሲታይ መመልከቱ ፣
እይጠቅምም በቃ ለአብዮቱ ፣
ታጋይ ሞተ እያሉ ማንሳቱ »
በቃ እንታገል ቢርከራሲውን ፣
ቅጥር ነፍሰ ገዳይ ሊቃቂውን ፣
የደረ ሕዝቦች ጠቢታውን ፣
የጭቁኖች ጠላት ጨምላቃውን ፣
የአብዮት ቀልባሽ እስተባባሪ የሆነውን »
ፀረ ሕዝቦች ዙሪያችንን ቢከቡንም ፣
አድኃሪው ቢርከራሲ ከቀኝ ኃይሎች ጋር ቢያብርም
አደር ባዩ ከሲግራቹው ሥር ቢነጠፍም ፣
እኛ እንሰግድም ፣ እናጉበድድም ፣
ሰፈውን ሕዝብ እንከድም ፣
እንታገላለን በሀቡዕ ፣ ሲያመቸንም በይፋ
አብዮታችን እንዲፋፋ ፣
የታጋይ ጓዶች ነፍስ በቀኝ ኃይሎች እንዳይጠፋ
እንሞታለን ፣
እንበዋለን ፣
በአቋማችን እንጽናለን »
አብዮቱን ለማፋፋም ፣
ቢርከራሲን ለመጽዳም ለማንበርከክ ፣
ፅረ ሕዝቡ እንዲጠፉ ፣
አብዮቱም እንዲገፋ ፣
ዲሞክራሲ ለጭቋኖች ያለገደብ ይለቀቅ በይፉ »
እንላለን እኛ ጭቁኖች ፣
የአብዮቱ አካል ታጋይ ዓዶች ፣
ምስኪን ተጨቋኝ መህደሮች »

አዲስ ዘመን ጎላር ፯ ቀን ፲፱፻፸ ዓመተ ምሕረት

ታጋይ ለዲሞክራሲ ፤ አድርባይ ለፍርፋሪ ፤

—ክአብርሃ አደቀልሰም

በአብዮት መድረክ ላይ ካለፈው ሳምንት ጀምሮ ስለዲሞክራሲ መብቶች የተያያዘው ውይይት ከሰማይ እንደመና የወደቀ የጹብ ዕዳ እንዳልሆነ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ትርታ የተከተለ ሁሉ የሚያውቀው ነገር ነው ። ውይይቱ ልክ በስመ «ዋሬቱ» ይካሔድ እንጂ ፤ በይዘቱ ለብሔራዊ ዲሞክራሲው አብዮት ፕሮግራም ስምረት ባሚታገሉ ኃይሎችና ይህን ፕሮግራም ለመከለስና ለመቀልበስ በሚሯሯጡት አካባቢዎች መሐል የሚካሔድ የርዕዮተ ዓለም ጦርነት እንደሆነ የሚሳት አይደለም ። በመሆኑም ለአብዮታችን ድል መምታትና ለሰፊው ሕዝብ መብቶች መከበር የሚቆረቆሩት ፤ የሚታገሉትና በየቀኑ የሚዋደቁለት ጓዶች በመካሔድ ላይ የሚገኘው ውይይት የሚከነክናቸውንእጂ በቸልታ ዓይን የሚመለከቱት አይደለም ። ሆኖም ግናቸውም ከስተት ሁለት ጉዮች እንዳለው ሁሉ፤ ምንም እንኳ ውይይቱ የተቀሰቀሰው የርዕዮተ ዓለም ቅልሰጎን ለማስተናገድ ቢሆንም ፤ ይህ ኢጋጣሚ ሰፈውን ሕዝብ በዲሞክራሲ ዋያቄ አካባቢ ለመቀስቀስና አድርባዮችንና አስመ ሳዩ ተራማጆችን በቅሙ ለማጋለጥ የሚያስችል በመሆኑ ፤ ተራማጆች የመጠቀም ግዴታ አለባቸው ። ባለ ቸው የንቃት ዋራትና የሰፈው ሕዝብ እጋር ተመክቱው አድርባዮችንና የኢ-ሕ-ሉ-ፓ ሠርጎ ገቦችን ለማው ደም እንደሚችሉም አያጠራጥርም ።

ተራማጆች በውይይቱ ቢሳተፉም የውይይቱ ባጸሪና የአለውን የኃይል ሚዛን ጠንቅቀው ማወቅ አለባቸው። ዛሬ በአብዮት መድረክ ላይ ነፃ የሆነ ውይይት ይካሔዳል ብሎ መገመት ዋኝነት ነው ። ደርግ ይህንን እንደማይፈቅድ ፤ እንዲሁም አድኃርያን ዋቅ ግቸው ሊነካባቸው ውይይቱን ከማፈን እንደማይመለሱ መታወቅ አለበት ። ምን ማለቱ እንደሆነ ላስረዳ ።

ሰፈው ሕዝብ በዚህ ውይይት እንዳይሳተፍ አድኃርያን እየተቅበዘበዙ ናቸው ። እንደሚታወቀው ሙ-ኢ-ሠማ ፤ የሸዋ ክፍለ ሀገር ሙ-ኢ-ማና የአዲስ አበባ የቀበሌ አጠቃላይ ባወጡት የጋራ መግለጫ «የዲሞክራቲክ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አውኑ» እንዲሉቀቁ በውሳኔያቸው ጠይቀው ሳለ ፤ አበመላይ ተራማጆችና የደርግ ቀኞች አንድ ላይ በማበር ና በቢሮክራሲው መሣሪያነት ውላ እው ለሕዝብ በሚሠራዋበት ጊዜአን ዲሞበረበር ተደርጓል ። ወደፊትም የሰፈውን ሕዝብ ድምፅ ለማፈንሲባል ይህን የመሰሰሉ በሥልጣን የመባለ ግና ቅሌታም ርምጃዎች አይወሰዱም ብሎ መጠበቅ አይቻልም ። በተለይም የዲሞክራሲን መሰቀቅ የሚቃወሙ ኃይሎች የውይይቱ አዝማሚያ ከከፋ ቸው ከእንዲህ ከሉሎችም ፀረ ሕዝብ ድርጊቶች እንደሚይመለሱ መታወቅ አለበት ።

ወደጽሑፌ ዓላማና ይዘት ልመጣ። የብሔራዊው ዲሞክራሲያ አብዮት ፕሮግራም በተግባር እንዲተረጉም ከሚታገሉት ኃይሎች መሐል እንደ መሆኔ መጠን ፤ በድብቅና በሹልክታ የርዕዮተ ዓለም ቅልበሳ ሲካሔድ ወይም ሲቃጣ ዝም ለማለት የምችል ስላልሆንኩኝ ፤ ብሔራዊው ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም ሥራ ላይ ለማዋል በሚደረገው ትግል ፤ በወደ ቁት ታጋዮችና ጭቁኖች ደም የተነከረውን አርማ በማንሣት ፤ ዛሬ በርዕዮተ ዓለም ድርቫ በአብዮታችን ሆነ በትግል አቅጣጫችን ላይ የተቃጣውን ኀና የተዘየደውን «ረቂቁ» የቅልበሳና የብረዛ ሙከራ ለመቋቋም ቆርጪ ተነ ሥቻለሁኝ። በተለይም ይህችን ጽሑፍ ለማበርከት የተነሣሣሁት ፤ በጥቅምት ፲፰ ፲፱፻፸ ዓ ም በአዲስ ዘመን ላይ «የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ—ላይ ንሳዊ አቀራረብ» በሚል ርእስ ከአቶ አስክዳር የቀረበውን የኢ-ሕ-ሉ-ፓን አቋም የሚያንፃባርቀውን የቅልበሳና ከለላ ጽሑፍ በቅሙ ማጋለዋ አስፈ ላጊ መስሎ ስለታየኝ ነው ። ምክንያ ቱም «ቀማጣን ቆጣጣ ካላሉት አብሬ ልፈትፍት ይላል» እንዲሉ የአቶ አስክ ዳር ኢ-ሕ-ሉ-ፓነት ዝም ብሎ ከታ ስፈ የውይይቱ መንፈስ ሊበረዘና ለቀ ልባሾች እጮች ሁኔታ ሊፈጥር እን ደሚችል አያጠራጥርምና ።

አቶ አስክዳር ጽሑፉን በሁለት ከፍ ሎታል ። በመጀመሪያም ክፍል ስለ ዲሞክራሲ ምንነት እንዳንድ ግምቶ ችን ለማስቀመጥ ይሞክራል ። ግን እምብዛም የተሳካለት አልመሰለኝም ከዚህ በፊት ስለዲሞክራሲ ከተጻፉት ጽሑፎች እንዳንድ ግምቶችን ገል ብጦ ፤ እሳያቸው ላይ የራሱ የሆኑና የቲዎሪ ስእሎቶችን ነስንሶ «በዚሁ ዋያቄ ላይ ማርክሲያዊ የሆነውን ትን ተና አቅርቤያለሁኝ » ይላል ። እኔ እንኳ «ሳይንሳዊ አቀራረብ» የሚለ ውን አርእስቱን ስመለከት ብዙ ያስ ተምረናል ብዬ ጠብቄ ነበር ። ወንድ ማችን ያለ አግባብ አሳፈረኝ እንጂ ! ለማናቸውም «በሳይንሳዊው መንፀ ያው» ውስጥ የሚሠነዝራቸውን እን ዳንዱን የቀዛቡ ፅንሰ ሐሳቦቹንና አብ ባሎቹን እንመልከትና ፤ አቶ አስክዳር እንደሚከተለው ሲጽፍ እናነኝዋለን።

«በባሪያ አሳዳሪ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሚኖረው ዲሞክራሲ የነገር መደብ መግልገያና በባሮች ላይ እምባ ገንንነት መዘርጊያ ነው ። በፊውዳል ሥርዓት ማኅበር ያለው ዲሞክራሲ በሌሎች መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍ ሎች ላይ እምባገነንነትን መፈጸሚያ ነው ። (ስርዝ ከእዕ) በከበርቴው ሥር ዓት ••••••••

አቶ አስክዳር ብዕሩን በማንሣት ወደመሮጥ አስቀድሞ በእዲስ ዘመን ላይ የወጣውን «ስለዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ—ላይ ንሳዊ አቀራረብ» በሚል ርእስ ከአቶ አስክዳር የቀረበውን የኢ-ሕ-ሉ-ፓን አቋም የሚያንፃባርቀውን የቅልበሳና ከለላ ጽሑፍ በቅሙ ማጋለጥ አስፈ ላጊ መስሎ ስለታየኝ ነው ። ምክንያ ቱም «ቀማጣን ቆጣጣ ካላሉት አብሬ ልፈትፍት ይላል» እንዲሉ የአቶ አስክ ዳር ኢ-ሕ-ሉ-ፓነት ዝም ብሎ ከታ ስፈ የውይይቱ መንፈስ ሊበረዘና ለቀ ልባሾች እጮች ሁኔታ ሊፈጥር እን ደሚችል አያጠራጥርምና ።

አቶ አስክዳር ጽሑፉን በሁለት ከፍ ሎታል ። በመጀመሪያም ክፍል ስለ ዲሞክራሲ ምንነት እንዳንድ ግምቶ ችን ለማስቀመጥ ይሞክራል ። ግን እምብዛም የተሳካለት አልመሰለኝም ከዚህ በፊት ስለዲሞክራሲ ከተጻፉት ጽሑፎች እንዳንድ ግምቶችን ገል ብጦ ፤ እሳያቸው ላይ የራሱ የሆኑና የቲዎሪ ስእሎቶችን ነስንሶ «በዚሁ ዋያቄ ላይ ማርክሲያዊ የሆነውን ትን ተና አቅርቤያለሁኝ » ይላል ። እኔ እንኳ «ሳይንሳዊ አቀራረብ» የሚለ ውን አርእስቱን ስመለከት ብዙ ያስ ተምረናል ብዬ ጠብቄ ነበር ። ወንድ ማችን ያለ አግባብ አሳፈረኝ እንጂ ! ለማናቸውም «በሳይንሳዊው መንፀ ያው» ውስጥ የሚሠነዝራቸውን እን ዳንዱን የቀዛቡ ፅንሰ ሐሳቦቹንና አብ ባሎቹን እንመልከትና ፤ አቶ አስክዳር እንደሚከተለው ሲጽፍ እናነኝዋለን።

«በባሪያ አሳዳሪ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሚኖረው ዲሞክራሲ የነገር መደብ መግልገያና በባሮች ላይ እምባ ገንንነት መዘርጊያ ነው ። በፊውዳል ሥርዓት ማኅበር ያለው ዲሞክራሲ በሌሎች መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍ ሎች ላይ እምባገነንነትን መፈጸሚያ ነው ። (ስርዝ ከእዕ) በከበርቴው ሥር

ዓት እንደሳይገስ ይቆጠራል ።ምንም ትርጉም ከሌላቸውና በየቦታው ለማ ንሜ ከተልጠፉት አባባሎች የፈካውን ለእንባብያን ልዋትና አቶ አስክዳር፤ «በከበርቴው ሥርዓት ያለው ዲሞክ ራሲ ምንም እንኳን በይዘቱ ከሌላ ከ በሩት ሥርዓተ ማኅበራት ባይለይም፤ ግለትም ዋቂቶች በብዙኃት ላይ ለም ባነኑንታቸውን የሚያነግቡበት ቢሆ ንም ፤ እንደፖለቲካል ፎርም የተጠቀ መበት የከበርቴው መደብ ነው።ይላል።

ይህ አባባል ምን ማለት እንደሆነ ፤ሚያውቁት አላሀና አቶ አስክዳር ብቻ ናቸው ። ከሰብአውያን ፍጡሮች ችሎታ በላይ ነውና ። እኔ በበኩሌይህ ንና ይህን የመሳሰሉትን አባባሎች ለአቶ አስክዳር ብዬ ለመረዳት ብሞ ክር ፤ ብል ብል ፍጭ የለሽ የበዶ ቃላት ጋጋታ ሁነው አግኝቼያቸዋለሁኝ ። እንደመሰለኝ ፈሪሳውያን በአኳኋና ቸው ከሁሉም የበለጠ ቅዱሳዊ ለመ ምሰል እንደሞከሩት ፤ አቶ አስክዳርም ያሸበረቁ ግን ባዶ ቃላትን በመዝር ዝር ፤ ከሁሉም የበለጠ ሳይንሳዊ ለመ ምሰል ፤ ሊቅነቱን ለማሳወቅ ይሞክ ራል ።

የአቶ አስክዳር ጽሑፍ ሁለተኛ ከፍል ደግሞ የኢትዮጵያ ሁኔታና ፋግርክሲዝምን(ያልተጋጋረውን !! ለማነናዘብ የሚሞክርበት ክፍልሲሆን የርሱ ሳይንሳዊነት ፈጽሞ የሚያክት ምበት ክፍል ነው ። በመጀመሪያው ክፍል እያነከሰ የመጣው ሳይንስ ፣ ፍጹም የሚሽመደመድበት ቤንዚን እንዳለቀበት ሙኪና ተፍ ተፍ የሚል በት ክፍል ነው ። እስቲ ሲፈራጥ እን መልከተው ።

የአቶ አስክዳር ዋና ፊየቲዎሪ የመ ከራከሪያ ነጥብ ፤ ለአቶ አስክዳርመነሻ የሆነው ዲሞክራሲ የመንግሥት ገጽታ ነው የሚለው ግምት ነው ። በመሠ ኖም ይላል አቶ አስክዳር ፤ የጹርው አድኃሪ ቢርክራሲ አስክ ልተደመ ሰሰ ድረስ የሰፈው ሕዝብ ዲሞክራ ቲክ መብቶች ሊከበሩ አይችሉም ። ደርግም የቅቁኖች መንግሥት ስላል ሆነ ዲሞክራሲ ያውጃል ብለን መጠ በት ፤ ለዚሁም መታገል የለብንም ።

ለው የዲሞክራሲ ዓይነት በነገርቢኝ እንዲያው በዋቂ ! በማሙ ነው የምሣ ጽንህ !

አቶ አስክዳር ቲዎሪ ብሎ የሚቆጥ ረው ከሩቅ ሆኖ የዲሞክራሲን ዓይነት መለየት መቻል ብቻ ሳይሆን ፤ ፍች የለሽ ባዶ ቃላትም መሠርጸር በርሱ

ይልቀንስ ዲሞክራሲን «በትግላችን» ለማግኘት መብር አለብን ። ቢሆ ኑም ቢሆን የእቶ አስኬዳር መሪታዊ ሕላፅና የክርክር ነጥብ ይዘ ሲሆን ፣ የዚሁኑ እዛባል ሊሳይንቲስት ለማ ስራዳት ከቶ እስኬዳርን እየጠቀሱ ጠቃ ቹቱ ስለሚሻል ፣ ክርሱ እየጠየቅሁኝ ይሆንኑ ለማሳየት እሞክራለሁኝ ።

« በማርክሲያውያን ዲሞክራሲና መንግሥት ተነነጥተለው ሊታዩን ከቶ አይችሉም - - - በኢትዮጵያ ዛሬ ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት የሕ ዝብ መንግሥት እንዳይደለ ለማንም ግልጽ ነው ። በሰላ በሕል ደግሞ የመ ንግሥት ቁንጮ የያዘው ጊዜያዊ ወታ ደራዊ አስተዳደር ደርግ የሕዝብ ጠላት አለመሆኑ ያንኑ ያህል የታወቀ ነው። እንዲያውም በሰፈው ሕዝብ ሙራሪ ትግል ግፊት የተነግ በመሳኘ ወቅቶች ከስፈው ሕዝብ ጋር መቆሙንና ትግ ለንም የሚያገዙ በርከት ያሉ መሠረ ታዊ ርምጃዎች መውሰዱን እናያለን። ያም ሆኖ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳ ደር ደርግ በመሠረቱ የንውስ ከበርቴ አስተዳደር ፣ ግን ምንሙ ዝንባሌ ያለው የንውስ ከበርቴ አስተዳደር ከመሆን አያልፍም ። በሰላ በከፉ ደግሞ በየ ካሲት ጀኔ የፈነዳው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ አብዮት የፈላጭ ቆራጭነን የን ይል ሥላሴ መንግሥት ቁንጮ ሊገረ ሰስ ቢችልም ፣ ሥላው የፊውዶ በር ሂው የመንግሥት አካል ግለትም ቢሮክራሲው ፣ መደበኛ ሙሩ ፣ ፖሊሱ ወዘተ - - - አልተደመሰሰም ። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍኑን የዲሞክ ራሲ መብቶችን ሊቀጻጀና ሊያሰከ ብር የሚችለው አውን ያለውን የመን ግሥት አመታር በሕዝባዊ ትመኔ ደም በሰ በሞተኩ የራሱን መንግሥትሲመ ሠርቅ ብቻ ነው ። »

አቶ አስኬዳር ዲሞክራሲና መንግ ሥት ተነነጥተለው ሊታዩን ከቶ አይ ችሉም ይበል እንጂ ፣ የዚሁኑ አዛባል ምንነት በቅሙ የተረዳው አይመስለ ችም ። እረ ለመሆኑ እነሱኒን ዲሞክ ራሲ የመንግሥት ገጽታ ነው ሲሉ ምን ማለትሞው ነው ፣ እነማርክስና ሌኒን ዲሞክራሲን መነጣጠል አይች ለም በሌም ቅሉ ወደኢትዮጵያ ሁኔታ ስመጣ ግድረን እንደሚገባው ሥልጣን የጨበጠው ፕር ሊጠየም ከሚችልባቸው የእገዛ ዘይቤዎች አንዱ ነው ግለታቸው ነው ። ሳስረዳ እንደምሳሌ የክርርቱውን መደብ እን ውሰድ ። የክርርቱው መደብ ሥልጣን በያዘበት አገር ውስጥ እንደሆነ ሶቪ ያል ፣ ኢኮኖሚክስና ፖለቲካል ውሳኔ በመጨረሻው ደረጃ እንደመደብ ትግሉ ውጤታ የበላይነትን ሊያስጠ ብቅ በሚችልበት የአገዛዝ ዘይቤይጠ ትግል ። ለምሳሌ እንደሁኔታው በክ በርቴው ዲሞክራሲ በቁጪዝም ፣ በቦ ነፖርቲዝም ፣ ወዘተ - - - እየለየው ሊጠቀም ይችላል ። የሰፈው ሕዝብ ትግል ያሰጋው እንደሆነ የሰፈውን ሕዝብ ዲሞክራቲክ መብቶች ሽር ጭርን በሆነ ቀሺስታዊ አገዛዝ የበላ ይነቱን ለማስከበር ይተራል ። ሁኔታ ውም ሲፈቅድለትና ሕዝቡ ለዲሞክ ራሲ የሚያካሔደው ትግል ሲያይል ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ይለቃል። ግለትም እንደገና ለመድገም ፣ ዲሞ ክራሲ የመንግሥት ገጽታ ነው ሲባል ከገርው መደብ ሊጠቀም ከሚችልባ ቸው የአገዛዝ ዘይቤዎች አንዱ ነው። ከገርው መደብ ባሕር ጋር በቅርብ የተያያዘ ነገር ግለት ነው ። በእ ንግሊዝኛ The loom of rule የተሰ ኙት ግርክሲሲቶች የሚጠቀሙ ባቸው ቃል ይሆንኑ በገርው መደ ብና በዲሞክራሲ መሕል ያለውን ግን ኙነት የሚያመለክቱ ናቸው ።

የፊደላትን ጥቂ ሳያውቁ በቃል እዋ ንተዋቸው እንደሚደጋግሞቸው ሕናን አቶ አስኬዳር ጀሀ ጊዜ ዲሞክራሲ የመንግሥት ገጽታ ነው ቢልም የዚ ሁኑ ትክክለሃ አባባል ምንነት አልተ ፈጸውም ። የዲሞክራሲን ጥያቄ እንደ ሚገባው ከገርው መደብ ባሕርና ከሌ ገዛዝ ዘይቤ ጋር ከማነናኘት ይልቅ ፣ ባልሆነ መንገድ ከመንግሥት አውታ ሮች ግለትም ከቢርክራሲው ፣ ከመ ብት የለሽነት ወደዲሞክራሲው ሊሸ ጋገር ችሏል ። በአቶ አስኬዳር እንጋ ገር ፅጠቀምና የዲሞክራቲክ መብ ቶች አመርቃሚ በሆነ እድገት ሲፈ ጠሩ ችለናል ። ይህ ምሳሌ በቲዮሪ ደረጃ የሚያስገን ፣ የዲሞክራሲን ጥያቄ የመንግሥትን ሥልጣን ከጨበጠው ደርግ ጋር በግ ያያዝ ፈንታ ፣ የዲሞክራሲን ገጽታና ደርግን ነጣጥሉ ፣ የዲሞክራሲንጥያቄ ከቢርክራሲው ጋር በማያያዝ ቢርክ ራሲው አስካለ ድረስ የዲሞክራቲክ መብቶች ሊኖሩ አይችሉም ይላል ። ለአቶ አስኬዳር ለዲሞክራሲ መኖርና አለመኖር መሰኙ የገርው መደብ ባሕ ሪና ሰፈው ሕዝብ ለዲሞክራሲ የሚ ያካሒደው ትግል ሳይሆን ፣ የመንግ ሥት አውታሮች መደምሰስ ወይንም አለመደምሰስ ነው ። በሰላ አነጋገር ከዴሮው ሥርዓት የተወረሰው መደ ብኛ ሠራዊት ፣ ፖሊስ ቢርክራሲ እስ ካልተደመሰሰ ድረስ የዲሞክራቲክ መብቶች ሊኖሩ ወይንም ያሉት ክፍ ተኛ የንይነት ለውጥ ሊያሳዩ አይች ሉም ።

አቶ አስኬዳር እንደሚለው ሳይሆን የዲሞክራሲ ጥያቄ ከገርው መደብ ባሕርይ ጋር እንጂ ከቢርክራሲው ጋር በቀጥታ አለመያያዙን አንድ ታሪካዊ ምሳሌ ልስዋ ። የፈረንሳይን አብዮት እንውሰድ ። እንደሚታወቀው በ፲፯ ኛው ክፍለ ዘመን በተካሔደው ታላቁ የፈረንሳይ ከበርቴ አብዮት ፣ የፈረን ሳይ ከበርቴ መደብ የፊውዳሉን አገ ዛዝ በመገርሰስ የራሱን ዲሞክራሲ ያዊ የሆነ የበላይነትን መሠረተ ።በሳ ቢያውም ሰፈው የፈረንሳይ ሕዝብ የከበርቴ ዲሞክራቲክ መብቶችንተጥ ናጨ ። ይህ ሁሉ እየሆነ ግለትምበፈ ረንሳይ የከበርቴ ዲሞክራሲ ሲሰፍን ከፊውዶው አገዛዝ የተወረሰው ቢር ክራሲ አልተደመሰሰም ። እንዲያውም የፈረንሳይ ከበርቴው መደብ የንበረ ውን ቢርክራሲ በማረት የራሱን ሥር ዓት በማስከን ተጨቅሞበታል ። ግለ ትም የፈረንሳይ ሕዝብ ምንም እንኳ ቢርክራሲው ባይደመሰስም ፣ ከመ ብት የለሽነት ወደዲሞክራሲው ሊሸ ጋገር ችሏል ። በአቶ አስኬዳር እንጋ ገር ፅጠቀምና የዲሞክራቲክ መብ ቶች አመርቃሚ በሆነ እድገት ሲፈ ጠሩ ችለናል ። ይህ ምሳሌ በቲዮሪ ደረጃ የሚያስገን ፣ የዲሞክራሲን ጥያቄ

በቅርብና በተብቅ የተያያዘው ሥል ጣን ከጨበጠው መደብ ባሕርይ ጋር መሆኑን ዲሞክራሲ የገርው መደብ የአገዛዝ ዘይቤ መሆኑን እንጂ እቶ አስኬዳር ለማሳየት እንደሚከጅለው በተቃራሚ ደረጃ ከቢርክራሲው ጋር የተያያዘ አይደለም ። ወይንም እነግ ርክስና ሌኒን ዲሞክራሲ የመንግሥት ገጽታ ነው አሉ እንጂ የቢርክራሲው ገጽታ ነው አላሉም ።

እዚህ ላይ ስለቢርክራሲው እንዳ ንድ ቃላት ጣል ማድረግ ይጠቅማል። ቢርክራሲው በመንግሥታዊው መዋ ቅር ውስጥ የገርው መደብ ፍላጎቱን በሥራ ለመተርጉም የሚያስችለው ታማኙ የሆነ አስፈጻሚ መሣሪያ ነው። በመሆኑም በተቅም ደፈኛና እስከተ ውሰነ ደረጀ ድረስ ከገርው መደብ ጋር የተሳሰረ ነው ። ቢርክራሲው የገርው መደብ መሣሪያ እንደመሆኑ መጠን አገልጋይ እንጂ የሀገሪቷን የፖለቲካል ቅርጽ ሊወሰን የሚችል ነገ የሆነና ራሱን የቻለ አካል አይደ ለም ። የገርው መደብ የዲሞክራቲክ መብቶች እንዲለቅ ከተደረገ ይህንኑ የ ጀያስደጽሞለት ቢርክራሲው ነው። እንዲሁም ገርው መደብ የዲሞክራ ቲክ መብቶችን ረግሞ ወደጉልበታዊ አገዛዝ ሲሸጋገር ፣ ይህንንም የሚያክ ናውስት ቢርክራሲው ነው ። ግለ ትም ቢርክራሲው አስፈጻሚ አካል እንጂ ሊኖር የሚችለውን መንግሥ ታዊ ቅርጽ በተቀጻጀ ደረጃ የሚወ ስን አይደለም ። እርግጥ በመደብይዘቱ የተነግ ቢርክራሲው እንደግናችውም አድጋሪ ኃይል የዲሞክራቲክ መብቶ ችን መኖር ሊቃወምና ሊረገር ይች ላል ። የተገኙትንም የዲሞክራቲክ መብቶች ለማጨናገፍ ይፍጨረጨ ራል ። ለማስተልበስም ይሞክራል። ቢሆንም ለዲሞክራቲክ መብቶች መኖር ወይንም አለመኖር ወሳኝ ምክ ንያት አይደለም ። ሊሆንም አይቻለ ውም ። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሁኔታን ብንወስድ ከሕዝቡ ትግል ሌላ ሰዲ ሞክራሲ መኖር ወይንም አለመኖር ወሳኙ አካል ደርግ እንጂ ቢርክራሲ አይደለም ። የመሬት ዓዋጁን የመሰለ ፍጹም አብዮታዊና ዲሞክራቲክየሆነ ርምጃ ብንወስድ ፣ በዚሁ ዲሞክራ ቲክ ዋያቄ ላይ ወሳኙ ኃይል ደርግ ሳይሆን ቢርክራሲው ቢ ሆን ኖሮ ይህ ርምጃ ባልተመሰደ ነበር ። ነገር ግን ወሳኙ ደርግ በመሆኑ ምንም እንኳ ቢርክራሲው ጎዋጁን በጽኑ ቢቃወ መውም ያ ፍጹም አብዮታዊና ዲሞ ክራቲክ የሆነው የመሬት ዓዋጅ በሕ ዝቡ ትግል አማካይነት ሥራ ላይ ሊውል ችሏል ።

የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያስገደብ አሁኑኑ !

ሰፈው ሕዝብ ያሸንፋል ።
(ይቀጥላል)

አዲስ ዘመን ነሃሪ ፮ ቀን ፲፱፻፸ ዓመተ ምሕረት ።

(ከአለፈው የቀጠለ) ከሕብሮቱ አይተለለዩም

ዲሞክራሲ የመንግሥት ገጽታ ነው ሲባል ፣ ገርው መደብ ለራሱ አገዛዝ ተስማሚ የሆነውን የዲሞክራሲ ዓይ ነት በሰጉ ፈቃደኝነት ይሠጣል ግለት አይደለም ። ለዚሁ የሰፈው ሕዝብ ትግል ያስፈልጋል ፣ ግለትም ሊኖሩት የሚገባቸውን ዲሞክራ ቲክ መብቶች ለማስከበርና ለመ ጠበቅ ሰፈው ሕዝብ መታገል ካለ በት ፣ እንዲሁም ዲሞክራሲ የመን ግሥት ገጽታ ነው ስለተባለ በእንዳ ንድ ሁኔታዎች የሚኖረው የዲሞክ ራሲ ዓይነት የመንግሥትን ሥል ጣን የያዘው ገርው መደብ ለመሥጠትና ለመቀቀድ ከሚችለው በላይ ሊዘል ትና ሲያልፍ አይችልም ። ለግለት አይቻልም ። በአንዳንድ ወሳኝ ወቅ ቶች በተለይም አብዮታዊ የሽግግር ሁኔታ ባለበት ጊዜ ሰፈው ሕዝብ ትግ ሉን በማፋፋም ገርው መደብ ከመ ደብ ባህሪው የተነሳ ሊፈቅድ ከሚ ችለው በላይ የዲሞክራቲክ መብቶ ችና ለመቀዳጀት እንደሚችል ተደ ጋግሞ በታሪክ የታየ ሀቅ ነው ። ግለ ትም ምንም እንኳ ዲሞክራሲ የመን ሥት ገጽታ ቢሆንም ፣ በሽግግር ወቅት ሕዝቡ በትግሉ ካለው መንግሥት ባህሪ ጋር የሚያጣጣመ ፣ ያለውን መንግሥት መደብ ይዘት የሚያራ የዲሞክራቲክ መብቶችን ለመጨና ጸፍ ይችላል ። የየካቲት ፷፮ አብዮት የመጀመሪያ ወቅቶች ለዚሁ በቂ ምስ ክር ናቸው ። ባላሳታዊው የአንዳል ካቸው መኳንን መንግሥት እያስ ሰራው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባካሔደው ወደር የለሽ ታሪካዊ ተጋድሎ የተነሳ ከዚሁ የመሳፍንት መንግሥት ጋር የሚያጣጥመው የዲሞክራቲክ መብቶ ችን እስከተወሰነ ደረጃ ድረስም ቢሆን ሊቀዳጅ እንደቻለ የሚታወቅ ነው ። አቶ አስክንድር ይህን ሀቅ ሰቶ ታል ። በመሆኑም ፣ ግለትም ይህን ሀቅ በመዘንጋቱ ፣ ምንም እንኳ ዲሞክ ራሲ የመንግሥት ገጽታና ገርው መደ ቦች ዲሞክራሲን የሚለቁት አፍንጫ ቸው ጋ እስከልደረሰም ቢሆንም ፣ በወሳኝ ወቅቶች ላይ ሰፈው ሕዝብ በትግሉ ይህን ደንበር ጥሶ ሰፋፊ የዲሞክራቲክ መብቶችን ሊቀዳጅ እን ደሚችል አልተረዳም ። ስለዚህም ነው ሊኖር የሚችለው ዲሞክራሲ መንግሥቱ ፣ ወይንም እርሱ እንደሚ ለው ቢሮክሰው ከሚፈልገው በላይ ሊያልፍ አይችልም የሚለው ።

ወደ ክርክራችን ዋና ነጥብ ልምጣ ። ይሽውም ባሁኑ ወቅት የዲሞክራቲክ መብቶች ለሞቁኖች ያስገደብ ሊኖሩ ይችላሉ ወይንስ አይችሉም የሚለው ጥያቄ ነው ። አቶ አስክዳር አይች ሉም ይላል ። እኔ ከሰፈው ሕዝብ ጉን ቁማ ፣ ከነመአሲማ ፣ መኢጣግና የአ-አ አጠቃላይ እና እንዲሁም ከሌሎች ተራማጅ ድርጅቶች ጋር ተሰልፈ ሊኖር ይችላል እላለሁ ። ይህንኑ አቋ ሜን ግለትም የዲሞክራቲክ መብቶች ለምን ሊኖሩ እንደሚችሉና እንደሚ ገባቸው የደርግን የመደብ ይዘታና የትግል ደረጃችንን በመዝርዝር ለማ ስረዳት እሞክራለሁ ።

አስቀድሞ «የዲሞክራቲክ መብቶች ለጭቁኖች ያስገደብ አሁኑኑ» የተሰ ኘው አብዮታዊ መፈክር ለነ አቶ አስክዳር ማስረዳቱ ሳይጠቀም አይ ቀርም ። ምክንያቱም በዚሁ መፍክር ላይ ከፍተኛ ውዥንብር ለመንዛት እየሞከሩ ናቸው ። ይህ መፈክር የሚ

ሰው የመጻፍ ፣ የመናገር ፣ የመሰብሰብ ፣ የመደራጀትና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት ለጭቁኖች ብቻ ባልተገደበእኩልነት ይሉቀቅላቸውማለት ነው ። ሕዝቡንም እነዚሁ መብቶች እንዲለቀቁ የሚያታግል መፈክር ነው። ይህ መፈክር የቡርጂ ዲሞክራሲ ጥያቄ አይደለም ። ግልጽ የሆነ አብዮታዊ የመደብ ይዘት ያለው ፣ መብት የሚጠይቀው ለሰፊው ሕዝብ እንጂ ለአድኃርያን አይደለም ። በሌላ በኩል ከሕዝባዊ ዲሞክራሲ ግለትም ሕዝባዊ ሥርዓት ተመሥርቶ ከሚኖረው ዲሞክራሲ በመለስ ነው ። ባይሆን ኖር እነ አቶ እስክዳር እንደሚረዱት ቢሆን «ማሽቆንቁሎኑ» ባሰፈለገ ነበር ። አቶ እስክዳር ደቀመዛሙርትም «ሕዝባዊ ዲሞክራሲ በተግል» ባሉ ነበር ። ምክንያቱም ሰፊው ሕዝብ ገና ሥልጣን አልጨበጠምና ቢሆንም የእነዚህ መብቶች መለቀቅ ሰፊው ሕዝብ ሥልጣን ለመረከብ የሚያደርገውን ዝግጅት ያፋጥንለታል ፣ ትግሉንም ያራምድለታል ። ያለገደብ የሚለው ቃል ፣ በመብቶቹ ላይ ማናቸውም ዓይነት ሕጋዊ ገደብት መደረግእንደሌለበት ያመለክታል ። ለዚሁም ያታገላል ። መብት ምንም ጊዜ ቢሆን ሊገደብ አይችልምና፣ አሁኑኑ የሚለው የመፈክሩ መጨረሻ ቃል ደግሞ የዲሞክራሲ መብቶች መለቀቅ ጊዜያዊና የአብዮቱ ሂደት የሚጠይቀው ነገር መሆኑን ያበስራል ። በአጠቃላይ«የዲሞክራቲክ መብቶች ለጭቁኖች ያለ ገደብ አሁኑኑየተሰኘው መፈክር የሰፊው ሕዝብ አምባገነንነት ገና ባልሰፈነበትና አብዮታዊ በሆነ ወቅት ወሳኝ ሊሆኑ የሚችሉትን የዲሞክራሲ መብቶች የሚጠቁም ፣ አብዮታዊ በሆነ መንገድ የሚያቀርብና አነርሱ የሚታገል መፈክር ነው ። በአጭሩ የመፈክሩ ይዘት ላይ እንደ ጠቀስነው ነው ።

እነዚሁ ዲሞክራቲክ መብቶች ሲኖሩ የሚያስችላቸውን ሁኔታ ወደ መመርመሩ ልሸጋገርና ከሩ ብዙ ዲሞክራሲ የመንግሥት ገጽታ ነው ያለው አቶ እስክዳር የዲሞክራሲን ጥያቄ ከደርግ ባህሪ ጋር ለማያያዝ እንዳችም ሙከራ እንዳላደረገ ማሳየቱና ማጋለጫ የሚታወስ ነው ። እስቲ ያላደረገውን ላድርግለትና የደርግን የመደብ ባህሪ ከዲሞክራሲ ጥያቄ ጋር ለማያያዝ ልሞክር ። እንደሚታወቀው ,በአብዮቱ ወሳኝ ወቅቶች ደርግ ከሰፊው ሕዝብ ጋር ተሰልፏል ። (በዚህም አባባል አቶ እስክዳር እንደሚስማኝ እተማመናለሁ ማለቴ እንደ አብዮታዊ ሲቆጠር ይችላል ። እንዲሁም ደርግን የመሰለ ተራማጅ የንውስ ከበርቴ ክፍል በዲሞክራቲክ አብዮት ውስጥ ሊሳተፍና የሚችል ዲሞክራቲክ ኃይል እንደሆነ ፣ ቢደንስ እስክቅርብ ጊዜ የሚያጠያይቅ አልነበረም ። በሰሞኑ የሚዶለትውን ከአቶ እስክዳር ይበልጥ የሚያውቅ አይደለም ። በመሆኑም ግለት ደርግ አብዮታዊና ዲሞክራቲክ ይዘት አለው ከተባለና እንዲሁም ዲሞክራሲ የመንግሥት ግዴታ ነው ከተባለ የጊ ውሉ ደርግ የሰፊውን ሕዝብ ዲሞክራቲክ መብቶች አብዮታዊ በሆነ መንገድ እንዲለቅ ሊደረግ የማይቻልበት ምክንያት ፈጽሞ አይታየኝም ። አቶ እስክዳር የመንግሥትና የዲሞክራሲ ጥያቄ ግደያዝ ይሰሃል ይህ ነው እንጂ፣ የባሙን የቀመን እየቀባጠሩ ያልሆኑትን ነገሮች መተብተብ አይደለም። አቶ እስክዳር ግን ምን ችገረው ፣ የዲሞክራቲክ መብቶች መለቀቅን እንደሚመር ስለሚፈሩ እነዚሁ መብቶች እንዳይለቀቁ በሆነውና ባለሆነው መንገድ እስከታገለ ድረስ ሌላው አያስጨንቀውም ። ያም ሆነ ይህ የአቶ እስክዳር የመከራከሪያ ነጥቦች እርሱን መልሰው እየመቱት ናቸው ።

ደርግ አብዮታዊና ዲሞክራቲክ ይዘት አለው ብለናል፣ በመሆኑም ሀቀኛ ተራማጅች የደርግን ባህርያና ያለንበትን ተጨባጭ ሁኔታ በማጤን ፣ ከጊዜው ጋር የሚሔደውን የአብዮታዊ ዲሞክራቲክ መብቶች ጥያቄ ያነሱት ግለ ትም «የዲሞክራቲክ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ» የተሰኘው መፈክር የደርግን ባህሪ በሚገባ የተረዳና ፣ ካለንበት ጊዜ ጋር የሚሔድ ነው ።

«የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ» የተሰኘውን መፈክር ከመሬት አዋጅ ጋር ለማመሳሰል ይቻላል ። ሁለቱም የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ጥያቄዎች ናቸው ። እንዲሁም ሁለቱም ከሥልጣን ጥያቄ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች ናቸው ። ደርግ ዲሞክራቲክና አብዮታዊ ይዘት ባይኖረው ኖር የመሬት አዋጁን ባላወጣ ዛሬም ሀቀኛ ተራማጆችና ሰፊው የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ የዲሞክራቲክ መብቶቻቸው ያለገደብ እንዲከበሩላቸው ባልታገሉ ነበር። በእንዳሩ የጨቋኖችን ዲሞክራሲ ያለገደብ የሚያንጸባርቁ ሚዲያዎች እማክኝነት እንዲሁም በሌሎች እጋጣሚዎች በከራሉም ቢሆን ታጥቋል ማለትም አብዮቱን የሚጠብቅ የታጠቀ የሕዝብ ከፍል አለ ። በአጭሩ ለዲሞክራቲክ መብቶችመኖር የሚበጅና እነዚሁን ለመጠበቅ በስ ተያርባቸው የቆመ የነቃ የተደራጀና የታጠቀ የሕዝብ ኃይል አለ ። ይህ ለኢትዮጵያ አብዮት ቆሚያለውን ትከከለኛውን መሥመር እከተላለውን የሚል የሚንቀው ወይንም ዙም ብሎ የሚያልፈው ነገር አይደለም ። ጎን ጨው አቶ እስክዳር ግን ይህ ከመጨፍ አልቆጠረውም ። ቢርከራሲው አስ ካለ የዲሞክራቲክ መብቶች አያኖ ሩም ሲል እነዚህ የቢርከራሲው ዘር የሆኑና የቢርከራሲውን አኛዋር ተቋቁመው ለዲሞክራቲክ መብቶች መኖር መሠረት የሆኑና እነዚህን ሊያ ስከብር የሚችል የነቃ ፣ የተደራጀና የታጠቀ የሕዝብ ክፍል መኖሩን ረስ ተታል ። ወይንም የሚያሸቅብበት አከባቢ ውስጥ ስለሆነ ራሱን ጋር ዲል ።

ሐ/ ለዲሞክራሲ መብቶች መኖር ሦስተኛው ወሳኝ ኃይል የሕዝቡትግል ነው ። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብትግል

ሁነኛና ጽኑ የሆነ ጎብረተሰብአዊ መሠ ረት ጥሏል ። የዲሞክራቲክ መብቶች ላቱቹን ግፊት እየሰባበረ ወደፊት የሚ ሞቀቅ ኃይል ነው ። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግሎን እያፋፈመ ወደ ፊት ሲራመድ በእንዳኑም የጠላት ኞን የመፈናፈኛ መድረክ እያጠበበ ሲመጣ የዲሞክራቲክ መብቶቹን በተሟሉበት ሲጮናጸፍ የማይችልበት ምክንያት የለም ። ልክ በእነ አንዳል ካቹው ጊዜ ሰፊው ሕዝብ በተሟሉበቱ አንዳንድ የዲሞክራቲክ መብቶችን ለማረጋገጥ ከመቻል የሚያግደው ነገር የለም ። የኢትዮጵያ ሐቀኛ ተራ ማጆች የሚታገሉትም ለዚሁ የተቀ ደሰ ዓላማ ነው ።

ማርክሳዊ ነኝ አያለ የሚፎልለው አቶ እስክዳር ግን ላይ ለማድረግ እንደሞክርኩት የኢትዮጵያ ተጨ ባሞ ሁኔታ በማጤን የዲሞክራቲክ መብቶች ሊኖሩ የሚችሉበት ሁኔታ ለመመርመር እንዳችም ዋሪት አላደ ረገም ። ተጨባጭ ጥናትን በአጠቃ ላይ ቃላት ለመተካት መሞከር ደግሞ ኢሳይንሳዊ ነው—ሌኒን ሄግልን በመ ጥቀስ ሳይንስ ተጨባጭ ነው ። ዲያ ኤክቲክስ የተጨባጭ ሁኔታ ተጨ ባጭ ጥናት ነው ። (Dialectics in the concrete study of concrete things) ያለውን መርሳት የለብንም ። አለበለ ዚያ እንደ አቶ እስክዳር በኢድያለ ዝም መቀመቅ ውስጥ ከመዋገሯት በኢሳይንሳዊው ባሕር ውስጥ ከመ ደፈቅ እንድንም ።

አቶ እስክዳር ቢርከራሲው አስክለ ድስ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍ ኮኖ የዲሞክራሲ መብቶችን ሲቀዳጅ አይችልም ይላል ። እንዶ አውነቱ ከሆነ ከፍተኛና ዝቅተኛ የሚለው ፍጹም የተምታታ ግምት ነው ። ሰርሱ አባባል አስካውን ድረስ የተገኙት ድሎች ዝቅተኛ ዲሞክራሲን ሲያ መለክቱ ፣ የመጻፍን ፣ የመናገርን ፣ መሰተ ... መብቶች ከፍተኛ ዲሞክራ ሲን ያበስራሉ—ግለትና የመሬት ዓዋጁን የመሰለ ፍጹም ዲሞክራቲክ አብዮታዊ ርምጃ ዝቅተኛ የዲሞክራሲ ዓይነት ሲሆን የመጻፍ የመናገር የመሰበሰብ መብቶች ግን ይዙቱ በከ ፍተኛ ደረጃ የሚገኙ የዲሞክራሲ መብቶች ናቸው ። በመሆኑ የመጀ መሪያምዕክ ግለትም ዝቅተኛቹ ቢሮ ክራሲው እያለ መገኘት ሲችሉ የኋለ ኞቹ ግለትም ከፍተኛ የዲሞክራሲ ዓይነቶች ዛሬ ቢርከራሲው እያለ ሊገኙ አይችሉም ይሰል ። እነን ፍጹም ግራ ያጋባኝ የመሬት ዓዋጁ እንዲት እንደዝቅተኛ ዲሞክራሲ የመጻፍ የመናገር ወዘተ መብቶች እንደከፍ ተኛ የዲሞክራሲ ዓይነት መታየታቸው ነው ። ተደናግሮ ግደነጋገር ይሏች ኋል ይኸ ነው ። ላስረዳ ። የመሬት ዓዋጁንና የመጻፍ የመናገር ወዘተ መብቶችን ብናነጻጽር የመሬት ዓዋጁ በታሪካዊ ከብደቱና ምንነቱ የሚበ ልጥና ከፍተኛ ደረጃ የሚይዝ መሆ ኑን ለመረዳት የሚያስቸግር አይደለም። ለምሳሌ እንድ በሰፊው ሕዝብ ትግል ለተወጠረ መንግሥት ፣ የመሬት ዓዋ ጁን የመሰለ ፍጹም አብዮታዊ ዓዋጅ ከመወሰድ ይልቅ ለሰፊው ሕዝብ የዲ ሞክራቲክ መብቶችን መልቀቅ ይቀ ለዋል ። ግለትም ንብረትን አሳልፎ ከመስጠት ፣ ሺህ ጊዜ የሰፈውንሕዝብ መብቶች መልቀቁን ይቀሰዋል ። በ፲ ፱፻፶፮ በሩሲያ የነበረውን የኬሬንስኪ መንግሥት እንውሰድ ። ይህ ለሰፊው ሕዝብ የዲሞክራቲክ መብቶች እንዲ ለትቅ የተገደደው የንውስ ከበርቴመን ግሥት ፈጽሞ የመሬት ዓዋጁን ለማ ውጣት አልደፈረም ። አልፈለገም ። አይችልምም ነበር ። ይህ ሆኖ ሳለ ፤ ግለትም የመሬት ዓዋጅ የዚያንያህል ከብደት ኖሮት አርሱ እንደዝቅተኛ ዲሞክራሲ ፣ የመናገር ፣ የመጻፍ ወዘተ መብት እንደከፍተኛ ዲሞክራሲ የሚ ታይበት ምክንያት አይታየኝም።እን ዲያውም ሰበብ አስባቡ የዲሞክራቲክ መብቶች መለቀቅን ለመቃወም ካል ሆነ በስተቀር ቢርከራሲው እያለ ሌላ መንግሥት እያለ ፤ የሰፊው ሕዝብ መብቶች ሊከበሩ እያችሉም የሚለው አባባል ምንም ቢሆን ትክክል አደደ ለም ። ኢሳይንሳዊ ነው ። ይህን ለማ ሳየት ከፍ ብዙ የጠቀስኩትን የሩሲያ ምሳሌ ተመልሼ ላንሳው ። እንደሚ ታውቀው በየካቲት ፲፱፻፲፮ የዛሩ መን

ግሥት እንደተገረሠሠ ፣ በአንድበኩል እርሱን የሚተካ የባላባቶችና የከበር ቴው ጊዜያዊ መንግሥት ሲቋቋም ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለረዥም ጊዜ በን ውስ ከበርቴዎች የበላይነት ሥር የነበ ሩት ሶቪዬቶች ተብለው የሚጠሩት መንግሥትና ሥልጣን የሚጋሩ ሕዝ ባዊ ድርጅቶች ተመሠረቱ ። ማለትም የሶቪዬቶችና የጊዜያዊ መንግሥትን ወኖራ የሆነ ‘መንግሥታዊ ሥልጣን ተቋቋመ ። ምንም እንኳ ጊዜያዊው መንግሥትና በንውስ ከበርቴዎች ተፅዕኖ ሥር የነበሩት ሶቪዬቶች የሰፊ ውን ሕዝብ ጥቅም ባይወክሉምና ከዛሩ የተመረሰው የ’ግግማሟ ቢሮ ክራሲ ገና ባይደመሰስም ፣ ሰፊው የሩ ሲያ ሕዝብ ባካሔደው ቆራጥና አብ የታዊ ትግል የዲሞክራቲክ መብቶ ቹን ያስገደብ ሊያስከብር ችሏል ። በዚ ያን ወቅት ሩሲያ ፣ አምን የተግማግማው ቢሮክራሲ እያለ ፣ ከሌሎች አገሮች ሁሉ የላቀ ዲሞክራሲ የነበራትከው ሉም ይበልጥ ነፃ የሆነች አገር ነበረች። በሉኒን አነጋገር ያኔ በሩሲያ ውስጥ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሠርኖ ነበር ። የዚያን ጊዜ ከሚኒስቶችና ተራማጆች የትግግማግው ቢሮክራሲ ሳይደመሰስ ሰፊው ሕዝብ ሥልጣን ሳይጨብጥ ፣ የዲሞክራቲክ መብቶች ያለገደብ እን ዲከበሩ እንታገልም ያለውን መንግ ሥትም ሥርዓት መመጸደቅ ነው አላ ሉም። ለዲሞክራቲክ መብቶች መኖር ወሳኙ የሕዝቡ ትግል መሆኑን በመር ረዳት ፣ የሰፊውን ሕዝብ ትግል በግ ፋፋም ሰፊው የሩሲያ ሕዝብ የዲሞክ ራቲክ መብቶችን እንዲቀዳጅ በግድ ረግ ለወሳኙ ፍልሚያ በወቅቱ እንዲ ዘጋጅ አድርገዋል ።

አቶ እስክዳር የዲሞክራሲ መብ ቶች ቢሮክራሲው ከተደመሰሰ በኋላ፣ ሰፊው ሕዝብ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ይላል ። ይህ አንድን ሰው በምንት ላቁ ለማስኬድ እንደመሞክር ነጋሪን ከፈረስ እንደማስቀደም ይሞክራል ። እንዲሁም ዲሞክራሲ የትግል ውጤት ብቻ ሳይሆን ፣ ራሱ የትግል መሣሪያ መሆኑን ይዘነጋል ። እንደሚታወቀው ቢሮክራሲው ለደመሰስ የሚቻለው በሕዝባዊ ዓመፅ ብቻ አይደለም ።ቢሮ ክራሲውን ለመደምሰስ ዲሞክራሲም ያስፈልጋል ። ቢሮክራሲውን ለማታ ለተ ፣ ሕዝብን በርሱ ላይ ለማደራጀት፣ እንዲሁም በቢሮክራሲው ውስጥያሉት ጭቁኖች ነቅተው እንዲደራጁና ከቢ ሮክራሲያዊ አሠራር ዘይቤ ተላቀው ሕዝቡን እንዲያነሳሱ ለማስተማር በግድ ዲሞክራሲ ያስፈልጋል ። ያስ ዲሞክራሲ በብትር ብቻ ቢሮክራሲ ውን እደመስሳለሁኝ ማለት ከሥሩ ከፍት በሆነ በርሜል ውሃ ለመሙላት እንደመፈለግ የሚቁጠር ሞኝነትነው። በእውነቱ ደግሞ የዲሞክራቲክመብ ቶችን መልቀቅ መታወም ነው። ቢሮ ክራሲው ከተደመሰሰ ወዲያ የዲሞክ ራሲ መብቶች ይለቀቁ ብሎ መላፋ ደድ ፣ ዛሬ በወሳኙ የትግል ወቅት ቢሮ ክራሲው እንዳይጋሰጥ ፣ እንዳይመታ እንደመፈለግ የሚቁጠር አድኃሪነት ነው ። በመንግሥትም ደረጃ እንደ ዚሁ ሰፈው ሕዝብ የመንግሥትን ሥልጣን ከያዘ በኋላ የዴሞክራቲክ መብቶች እንደሚኖሩ ዕውቅና የማያክ ራከር ሆኖ ሳለ ፣ ዲሞክራሲ ከሥል ጣን በኋላ ብሎ መድረቁ በላዶ ሚዳ መፈራጥ አንጂ ሌላ ትርጉም የለ ውም ። ጥያቄው ግን እርሱ እይደለም። ጥያቄው ሰፈው ሕዝብ ሥልጣንን ለመጨበጥ በሚያደርገው ታሪካዊተጋ ድሎ የዲሞክራቲክ መብቶች ያስፈል ጉታል ፣ ወይንስ እያስፈልጉትም ? ካስፈለጉትስ ለነዚሁ መከበር መታ ገል አለብን ወይንስ የለብንም ? አቶ እስክዳር ሊሸሽውና ሊያድበሰብሰው የሚሞክረው ጥያቄ ይህ ነው ። አቶ እስክ ዳር እያስፈልጉትም ለማለትባይ ደፋርም ። ሕዝቡ መብቶቹን ዛሬለያ ስጠብቅ አይችልም ይላል ። እኔ ግን ወሳኙ የሕዝቡ ትግል መሆኑን ስለ ማወቅ ፣ ሰፈው ሕዝብ ለዲሞክራቲክ መብቶች በተፋፋመ አኳኋን ለማታ ገል ከታገልን ፣ ከሕዝብም ጋርሆነን ለነዚሁ መብቶች መከበር ከተዋደቅንኒ እነዚህን የሰፈውን ሕዝብ መብቶች ለማስከበር እንደሚችል እልጠራጠ ርም ።

አቶ እስክዳር ኢሕአፓ ፣ ኢሕአፓ የሚሽተውም ስዚሁ ነው ። የእሕ አፓ ጥንብ አንጣው አቶ እስክዳር « ዲሞክራሲ ከድል በኋላ ፣ የኛ መን ግሥት ካልተቋቋመ ለዲሞክራሲያሚ ካሔደው ትግል ፋይዳ የለውም ፣ ያሥ እያለ የዲሞክራቲክ መብቶች ሊከበሩ አይችሉም » ወዘተ እያለ ከዚህ በፊት ኢሕአፓ በዲሞክራሲ ጥያቄ ፣ በመ ራት ጥያቄ ወዘተ - - - -የወሰዳቸውን አቋም ሲያስተጋባ ፣ የከረፋ ኢህአፓ ነቱን ሲያናሩ እይተናል ። የኢሕአፓ ሠርጎ ገቡ አቶ እስክዳር ርቃነ ሥጋ ውን የቀረውን የኢሕአፓ አቋሞአኳ ኩሎ መልሰ ቢያመጣም የታሪክ ትብ ያነቱን አይሸርም ። እዛው እመጣበት መመለሱ አይቀርም ። የጽሑፌ አር እስት እንደሚያመለክተውም ፤ሐቀኞ ተራማጆች የኢሕአፓ ሠርጎ ገቦች አብረውን እንዳይፈተፍቱ ፣ አስፈላ ጊውን ታሪካዊ ትምህርት ሰጥተው ከወደመጡበት እንደሚልኳቸው አል ጠራጠርም ። እንዴ ከመቱ ደኅናእደ ርገው መምታቱ ስለሚያስፈልግ የኢ ሕአፓ ሠርጎ ገቡን አቶ እስክዳርን እንደመጠባቸኛ ወደ ማጋለጡ ልገሥ ግሥና ፣ አቶ እስክዳር የዲሞክራቲክ መብቶች እንዲለቀቁ የሚታገሉትን ኃይሎች እንደሚከተለው ሲያጋል ጣቸው ። እንመልከተው ።

ፈይህ የማይቀረው ግን መራራ ትግል የሚጠይቀው እውነተ ገቢር ሳይሆን፣ በትግሉ ግግሽ ጉዳና ላይ በእዋጅ የዲ ሞክራሲ መብቶችን ለሚቀናች ያለ ገደብ አሁኑኑ በኋላ እመጣበታለሁ ። የሚጠይቁ፣ የመደብ ትግሉን በመደብ እርቅ ሕልም የተኙ ቡርጂ ዲሞክራ ቶችና እኔያ ረዥሙንና መራራውን ትግል እንደመር የሚፈሩ በዓዋጅና በሕሚናር ብቻ ጠላት እጅ እንዲሰጥ የሚያልሙ ከድል በፈት ሕገ መንግ ሥት የሚያስቀድሙ ለስላሳ «ሶሺያሊ ስቶች» ብቻ ናቸው።

ለውሩው በቡቱ ግጋለሙ ነመነ ራ ስን ግጋስዋ ይሉሃል ይሄ ነው ። ሳሳ ይህ።ዲሞክራሲ ለሚቁናች ያለገደብ የሚለው መፈክር አንተ እንደምትለው

የመደብ እርቅ መፈክር ሳይሆንየመ ደብ ትግል መፈክር ነው— አስቲ መፈ ክሩን በደንብ እድርገህ እየው። ለሚ ቁናች ብቻ ይላል። ግለትም ለእደህ ርያንና ለጨቋኞች መብቱን ይነፍጋል። በመሆነም ይህ መፈክር ጠላት መደቦ ችን የሚያቅቅር በመሀላቸው ያለውን ትግል የሚያፋፋም አንጂ አንተ እንደ ምትለው የሚያስታርቅ አይደለም ። ነገር ግን አንተ የተሰየየማንበብና የመ ረዳት ችሎታ አለህና አልፈርድብህም። ሁለተኛ አንተ እንደምትለው ዲሞክ ራሲ ለሚቁናች ያለገደብይሰቀት ግለት በሉ ዲሞክራሲ አሁን አግኝታችኋልና ጠላቶቻችሁን ይቅር ለእግዜር ብላችሁ ታረዳቸው ግለት አይደለም። አታውቀው ይሆናል እንጂ ዳሞክራሲ የትግል መገሪያ ትግልን የሚያፋፍምና ግለት የሚሠጠው መሣሪያ ነው ። ለሰፈው ሕዝብ ዲሞክራሲ ይለቀቅግለት ሰፈው ሕዝብ በተፋጠነ አኳኋን ይንቃ፣ ይደ ራጅ፣ ይታገል፣ ይንቀሳቀስ በአጭሩ ትግሉ ይፋፋም ግለት ነው እንጂ ትግ ሉን ግቀዝቀዝ አይደለም። ስለዲሞክ ራሲ «በትጓልቁ» ትናገራለህ እንጂ ምን እንደሆነ የምታውቀው አልመሰ ለኝም። ሌላም ነገር አለ ። ታስታውስ እንደሆነ (ምን ማስታወስ ብቻ አንዲ ያውም አብረሀም ሳትናርበት አልቀ ረህም) ጓዶችህ እነ ዓለማየሁ ሃይሌና ተፈሪ ባጎቴ የሰፈው ሕዝብ ዲሞክራሲ ጥያቄ በግረን የመደብ እርቅን ለማሳ ካት ገፍ ጉድ ይሉ ነበር። እምን አልሆ ነላቸውም፣ እናታቸው ላይ ተመቱ ። ዛሬ አንተ የነርሱን ጫካ ተከትለህል። ብቻ ወደ እነ አለማየሁ ልመለስና ከነ ርሱ ታሪክ ሰፈው ሕዝብ የሚግረው ዲሞክራሲን ግፈጋና የመደብ እርቅን ግውረድ በቅርብ የተያያዙ እንደሆኑ ነው አንጂ፣ አንተ አንደምትለው የዲሞ ክራቲክ መብቶች ቢለቀቁ መደቦች ይታረቃሉ አይደለም። አቶ እስክዳር ሌላው ቢቀር እኔ እንኳን አንተን ግጋ ለጪን እንደግላተው አትረዳም ።

አቶ እስክዳር የዲሞክራቲክ መብ ቶች እንዲከበሩ የሚጠይቁትን «ረዥ ውንና መራራውን ትግል እንደመር የሚፈሩ በዓዋጅና በሴሚናር ብቻ ጠ ላት እጅ እንዲሰዋ የሚያልሙ ናቸው» በግለት ሲያንጓጭሸቸው ይሞክራል። ይህን በሰፈው ሕዝብ ትግል እንደማ ኽፍ እቅተረዋልሁኝ—እነ ኮሎኔል ዳንኤል አስፋው፣ እነ ዶክተር ሰናይ ልኬነብዙ ጨቋ የሚቆጠሩ ከድሪዎች ታጋይኞች፣ ጭቁኖች- - - የዲሞክራቲክ መብቶች እንዲከበሩ ከጠላት ጋር ሲተ ናነቁ እንደተዋደቁ ዛሬም ብዙ ታጋ ዮች እንደሚሞቱለት ግን በነገራቸውነ ወንድም በታላቁ ወንበር ማሞትን ት ተህ ከቢሮህ ወጣ በልና እንዲያው ለነ ገሩ ሰፈው ሕዝብ የሚለውን እስቲ ለመስማት ሞክር። አንተ እንደምት ለው የዲሞክራሲ ጥያቄ የሲሚናር ጥያቄ ሳይሆን፣ ሰፈው የኢትዮጵያ ሕ ዝብ በጉርውና በትግሉ የሚያነግሠ መገሪያ ትግልን የሚያፋፍምና ግለት የሚሠጠው መሣሪያ ነው ። ለሰፈው ሕዝብ ዲሞክራሲ ይለቀቅግለት ሰፈው ሕዝብ በተፋጠነ አኳኋን ይንቃ፣ ይደ ራጅ፣ ይታገል፣ ይንቀሳቀስ በአጭሩ ትግሉ ይፋፋም ግለት ነው እንጂ ትግ ሉን ግቀዝቀዝ አይደለም። ስለዲሞክ ራሲ «በትጓልቁ» ትናገራለህ እንጂ ምን እንደሆነ የምታውቀው አልመሰ ለኝም። ሌላም ነገር አለ ። ታስታውስ እንደሆነ (ምን ማስታወስ ብቻ አንዲ ያውም አብረሀም ሳትናርበት አልቀ ረህም) ጓዶችህ እነ ዓለማየሁ ሃይሌና ተፈሪ ባጎቴ የሰፈው ሕዝብ ዲሞክራሲ ጥያቄ በግረን የመደብ እርቅን ለማሳ ካት ገፍ ጉድ ይሉ ነበር። እምን አልሆ ነላቸውም፣ እናታቸው ላይ ተመቱ ። ዛሬ አንተ የነርሱን ጫካ ተከትለህል። ብቻ ወደ እነ አለማየሁ ልመለስና ከነ ርሱ ታሪክ ሰፈው ሕዝብ የሚግረው ዲሞክራሲን ግፈጋና የመደብ እርቅን ግውረድ በቅርብ የተያያዙ እንደሆኑ ነው አንጂ፣ አንተ አንደምትለው የዲሞ ክራቲክ መብቶች ቢለቀቁ መደቦች ይታረቃሉ አይደለም። አቶ እስክዳር ሌላው ቢቀር እኔ እንኳን አንተን ግጋ ለጪን እንደግላተው አትረዳም ።

አቶ እስክዳር የዲሞክራቲክ መብ ቶች እንዲከበሩ የሚጠይቁትን «ረዥ ውንና መራራውን ትግል እንደመር የሚፈሩ በዓዋጅና በሴሚናር ብቻ ጠ

መህል ነህ ።

አቶ እስክዳር ፀረ ዲሞክራሲውን ዘ መቻ በመቀጠል የሚከተለውን ይላል።

«ለስላሳ ሶሺያሊስቶች እመጣለ ችው ከግል » ነው። የሰፈውን ሕዝብ ብሶቶች ብሶታችን በማለት እየመሠ ደከማ ጉኑን ያውቃሉና በእወደድ ባይ ነታቸው ሰፈው ሕዝብ ሲያስፈልገውና ሲመኘው ቢኖር ያለመራራው ትግሉ ሊያገኘው የማይችለውን የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያስገደብ ደርግ ያውጅልን እያሉ ነው። እርግጥ ደርግ ዛሬ ወይም ነገ የዲሞክራሲ ዓዋጅ ሊያ ወጣ አይችልም ወይም አያወጣም አይ ባልም።»

አቶ እስክዳር ሀቀኛ ተራማጆችን «የሰፈው ሕዝብ ብሶት ብሶታችን ነው » እያላችሁ ትመሀላችሁ ታዲያ የሚያስመለማን እንጂ የሚያስወን ጅል አልመስለኝም » እርግጥ የሕዝቡ ብሶት ያንተ ላይሆን ይችላል ። እርሱም መቼም ሌላ ነገር ነው ።

አልበቃ ብሎት የሰፈው ሕዝብ ዲሞ ክራሲ ፈላጊነትን እንደ « ደከማ ጉኑ» ይቆጥረዋል።ላንተ ይሆን ይሆናል እንጂ የሰፈው ሕዝብ ዲሞክራሲ ፈላጊነት ደከማ ጉን ሳይሆን ጠንካራው ጉን ነው ። ላንተ ሁሉም የተገላቢጠሹ ነው።ለምን ይሆን ? እላይ ከአተ እስክ ዳር በጠቀስሁት አቶ እስክዳር ከፍተኛ የሌብነትና የማጭበርበር ሥራ ይፈጽ ማል ። ተራ ቅጥር ነፍሰ ገዳይነት ብቻ ሳይሆን ተራም ሌብነት አለው ። ለዲ ሞክራሲ መብቶች የሚታገሉትን ኃይ ሎች እነዚህን ያለመራራው ትግል ለመቀዳጀት ትፈልጋላችሁ የናንተ ፈለግ ትግል ሳይሆን ደርግን መመጻ ደቅ ነው ይላል ። አውነት (ፀረ ደርግ ብትሆን እንዲህ ስትል ባማረብህ ነበር !) «የዲሞክራቲክ መብቶች ለጭ ቁኖች ያለገደብ አሁኑኑየተሰኘውን መፈክር እንግበው የሚታገሉትን ሁሉ ተራማጆች መራራውን ትግል ትጀኛላችሁ ማለት «ከብት ባልዋ ለፀት ኩበት ለቀማ»እንደመሄድ የሚ ቀመር ሽንገላ ነው ። ራስንም ለት ዝብት አሳልፎ መስጠት ነው። ላይ ለማ ሳየት እንደሞክርኩትም የዲሞክራቲክ

መብቶችን ለማስከበር በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የሰፊው ሕዝብ ወገኖች መድቀቃል እያወደቁም ናቸው ። ይህ ምናልባት ለእንተ መሪር ላይሆን ይች ላል ። መፈክሩንም ብንመለከተው ደርግን የሚማጸን ሳይሆን ሰፊውን ሕዝብ ለእብዮታዊ አንባቢ ጥያቄና አጣዳፊ ተግባር የሚታገል አብዮታዊ መፈክር ነው ። ዲሞክራሲ ተነን መዲያ ሳይሆን ዛሬውኑ ለዲሞክራሲ እንታገል ደርግንም የሰፊውን ሕዝብ መብቶች እንዳያስከብር እናስገድደው የሚል መፈክር ነው ። እንተ እንደም ትፈልገው ደርግን በዲሞክራሲ ዋያቄ አትወትውቱት አትታገሉት የሚል አይደለም ። ለማናቸውም ትግል ትግል የሚለው የኢህአፓ ሠርጉ ገብ አቶ አስክዳር ስለዝሕብ ትግል የሚያ ስብውን በበቂ የተገነዘበው ይመስለ ናል ።

ከደርግ አዋጅ ትጠብቃላችሁ እያለ በተራማጆች ላይ ለመረባረብ የሚሞ ክረው አቶ አስክዳር (ላይ ከርሱ ከጠቀስኩት ለማየት እንደሚቻለው) አፉን እንደባልቱት በማሽሞተሞተ «ግን እምን » እኮ ደርግ የዲሞክራሲ አዋጅ ሊወጣ ይችላል ይላል ። ታዲያ ሊያወጣ ይችላል ካልህ የግታውቅው ፅንሰ ሀሳብ ውስጥ ገብተህ ያ ሁሉ ዝባዝንኬና ራስን ማጋለጥ ምን አመ ጣው ። ?

እንዲሁም ደርግ የዲሞክራሲ አዋጅ ሊያወጣ ይችል ይሆናል ። አይ ችልም አይባልም ካልክ ሕዝባዊ ሥርዓት ከተቋቋመ በኋላ ስለሚመሠ ረተው ዲሞክራሲ መቀባጠርህን አቁ መህ ዛሬ ደርግ ሊያወጣው ይችል ይሆ ናል ስለምትለው የዲሞክራሲ አዋጅ አቁምህን ግልጥልጥ ማድረግ አለብህ ደርግ የዲሞክራሲ አዋጅ ሊያወጣ አይችልም አይባልም ። ከተባለ ለሰ ፊው ሕዝብ መብቶች ቆመናል የሚ ሉት ተራማጆች በሙሉ ይህ አንተ ሊወጣ ይችላል ይሆናል ። ስለምት ለው አዋጅ መነሪክር በዚሁ አዋጅ አወጣጥ ላይ ተፅእኖዋቸውን ማሰማት ይህ አዋጅ አብዮታዊ ስልትና ሕዝ ባዊ ይዘት ኖሮት እንዲወጣ መታገል እንዳለባቸው የሚያከራክር አይመስ ለኝም ። ዛሬ የሰፊው ሕዝብ ዲሞክራ ቲክ መብቶች እንዲከበር የሚታገሉ ኃይሎች ወደፊት የሚራመዱት ይህን አቋም ይዘው ነው ። እንዳንተ ከደርግ አዋጅ እንጠብቅም ግን እኮ ሊያውጅ ይችል ይሆናል ብለው ራሳቸውን አደ ነጋግረው ሌላውን እያወናብዱም ። ወደፊት ሕዝባዊ ዲሞክራቲክ ሥር ዓት ሲመሠረት ያኔ ዲሞክራሲ ይኖ ራል በሚለው ግምት ሳይወሰኑ የዲ ሞክራሲን ዋያቄ ወደትንቢት ሳያሸ ጋግሩ ዛሬ ሁኔታውና አቅማቸው እስክ ፈቀደላቸው ድረስ ለሰፊው ሕዝብ ዲሞክራቲክ መብቶች ይታገ ላሉ ። ይዋደቃሉ ። ይሞታሉ ።

የዲሞክራሲ መብቶች ለሞቱኖች ያለገደብ እሁኑ !

ሰፊው ሕዝብ ለዲሞክራሲ ለእብ የታዊ አመራር ለብሔራዊ ነፃነት !

እስመሳዮችና አድር ባይዮች ይመ ደማሉ !

ሰፊው ሕዝብ ያሸንፋል ።

(ይቀጥላል)

አዲስ ዘመን

ዋና አዘጋጅ

ብርሃኑ ዘርይሁን ።

ረቡዕ ጎንደር ፲፯ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓመተ ምሕረት ።

(ርእሰ አንቀጽ)

የከርከር ዘዴ በአብዮቱ ሠረር

ስለዲሞክራሲ ዋያቄ ፣ ከጥቂት ሳምንት ጀምሮ በአዲስ ዘመን አብ የታዊ መድረክ ላይ የሚደረገው ክርክር አንባቢ ያተኩረበት ክፍል መሆኑ የታመነ ነው ። የዲሞክራሲ ልምድና ባህል በሌለበት ሀገር በሕዝብ ፊት እንደጊህ በይፋ የሐሳብ መፋለጥ በ ሂደረግበት ጊዜ አልር አልር ግራ የመጋባት ሁናቴ ሊታይ ይችላል ። ለመግር ፣ ለመራመድ የሚሻ ማንኛውም ዜጋ ግን የዚህን መድረክ ጥቅም አይክደም ። ተራማጅ ኃይ ሎችም በከፍተኛ ጥንቃቄ ይከታተሉታል ። ስለዲሞክራሲ ዋያቄ ከዚ ህም ከዚያም የሚመጡትን ዋያቄዎች በመመልከት በግውጣት ፣ በግው ሪድ ትክክለኛውን ለመረዳት የሚሞክሩ ጥቂቶች አይደሉም ። ሆኖም ያንዳንዱ የከርከር ስልት ፣ ያንዳንዱ የስደብ ጋጋታ ያደናገራቸውና ግር ያሰኛቸው ደግሞ አሉ ። ንትርኩ ቀርቶ ፣ እንደላይንስ ቲዎሪ ተቃራኒ ሀሳቦች ጉን ለጉን ቀርበው አንባቢ አቋም እንዲወስድ ቢደረግ ይመር ጣሉ ። ይህ ሀሳብ በቅንነት ላይ የተመሠረተ ቢሆንም ፣ የሚካሔደው ትግል ርዕዮተ ዓለማዊ የመደብ ትግል አስከሆነ ድረስ በለስላሳና ሚና ባልለየ (ጀውኬራል) መንፈስ ሊከሔድ እንደማይችል መገንዘብ ያስፈ ልጋል ። የአንደን ሀሳብ ወይንም መሥመር ትክክለኝነት ለማሳየት የሀ ሳቡን ከመሠረታዊ መርሆ ጋር መያያዝ ብቻ መጣበጽ አይበቃም ። የተ ቃራኒውንም አስተሳሰብ ጽኮግነት ለመጠቆም ፖለቲካዊ ፍልሚያ ወይም ፖሌሚክስ የግድ አስፈላጊ ነው ። እርግጥ በፖለቲካው ትግል ውስጥ የንትርክና የስድቡ ብዛት ፣ እንዳንዴ የፖለቲካውን ክርክር የሚያበላሽና የሚያደበዝዝ መስሎ ቢታይም የፖሌሚክስን አስፈላጊነት መካድ አይ ቻልም ። እንዲያውም ኢትዮጵያ በዚህ የክርክር ስልት የተካኑ ተራማ ጆች እንዲኖራት ያስፈልጋል ።

ነገር ግን የፖሌሚክስ ዓይነት አለው ። የጠላትን ሠፈር ለመያም ሰስ የሚደረግ ፖሌሚክስ አንድ ዓይነት ነው ። ከአንድ ዓመት በፊት

በኢ· ሕ· አ·ፓ· ላይ የተደረገው ለዚህ ዓይነት ፖሊሚክስ አንድ ምሳሌ ነው ። ተገልጦ ከአብዮት ሠፈር እንዲተፋ ተደርጓል ። በወገን ኃይሎች መካከል የሚደረግ ፖሊሚክስ ደግሞ ንትርክን ያዘለ ቢሆንም በመጀ መሪያ በቅን መንፈስ አስተያየትን ከቀረቡና ትክክል መሆኑን ካሳዩ በኋላ የሚቃወሙት አስተያየት ምንና ምን ላይ እንደተሳሳተ በመጠቆም ከየትኛው የተሳሳተ አስተያየት፣ እንደመነጨና የትኛውን ዓይነት አድ ኃሪ ዝንባሌ እንደሚያመለክት እያስተማረ የሚያሳምን መሆን አለበት ። መንቀፍ ቢያስፈልግ ስንኳን ትክክለኛ አለመሆኑን ከሚጠቁም ፖለቲ ካዊ ነቀፌታ ግለፍ የለበትም ። ክርክሩ የሚካሔደው በወገን ሠፈር ውስጥ መሆኑን ጠንቅቆ በመረዳት ከአጉል እንካ ሰላንቲያና ቅጽል ከመለጣጠፍ መራቅ ያስፈልጋል ። ምክንያቱም የክርክሩ ውጤት እን ደኛው ሌላውን ረትቶ ግሳሙናና ሌላውም ስህተቱን ተረድቶ አቋሙን እንዲያስተካክል ማድረግ እንጂ ከትግሉ እንዲባረር ማድረግ አይደለ ምና ። ስለዚህም ፣ የአምባገነን የክርክር ዘዴን ፣ የአፋርቲያም የክርክር ዘዴን ፣ የአልሸነፍ ባይ ክርክር እርግፍ አድርጐ መተው ያስፈልጋል ። ከለበለዚያ ፖሌሚክስ የአብዮቱን ሠፈር በማጠናከር ፈንታ የሚያዳክም ሊሆን ይችላል ።

ወትሮውንም ቢሆን ከሠራዊቱ ዕድገት ወደኋላ መቅረት ከእምቢ ሪያሊዝምና ከኃይለ ሥላሴ ማምራ ጭፍጨፋ የተነሳ የተራማጆች ቁጥር በጣም ዝቅተኛ ነበር ። ከአብዮቱ መዲሀም ምንም እንኳን ቁጥራቸውን ሲግብዛት ብዙ ጥረት ቢደረግም ከውጭው ወረራ ከውስጡ ሁር ቡራ የተነሳ ብዙ ተራማጆች ፣ ብዙ ታጋዮች በየቀኑ በትግል መስክ ላይ እየወደቁ ኖቸው ። ስለሆነም የተራማጁ ሠፈር በጣም ጠባብ ነው ። በጣም አነስተኛ ነው ። የጠላት ሠፈር ደግሞ እጅግ ሰፊ ነው ። ስለሆነም ክርክሩ ንትርክ ያዘለ ፖሌሚክስ መሆኑ ባይቀርም የተሳሳተ መስመርን ለማስተካከልና የአብዮቱ ሠፈርን ለማጠናከር የሚረዳ እንጅ አስቦርግነ ከሠፈር የሚያስወጣ መሆን አይገባውም ። አለበለዚያ የአብዮቱን ሠፈር እናመነምነዋለን ። እናዳክመዋለን ። ብሎም ለቅልበሳ ምቹ ልናደርገው እንችላለን ። ማንም ተራማጅ ደግሞ ይሆንን ኢይመኝም ። ከዚህ በመለስ ግን ሁሉም ልክ ነው የሚለውን መሥመሩን ለማስረዳትና ሌላውን ለመርታት የሚያደርገው ፖሌሚክስ እየሞፈ መቀጠል አለበት ።

እንግዲህ እንደገባኝ ከሆነ የጎቡዕ ድርጅቶች መርህ ግብር የሚመስከተው ፣ በማርክሲስት—ሌኒንስት ድርጅቶች ውህደት የመዝ አደሩ ፓርቲ ከመውጣቱና ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ከመመሥረቷ በፊት ያለውን የትግል ወቅት የሚመለከት ይመስለኛል ። የመዝ አደሩ ፓርቲ ከተመሠረተ በኋላማ ፣ የነሪዎቹ ጎቡዕ ማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅቶች በየግል የሱም ። ተዋሕደው አንድ የመዝ አደር ፓርቲ ሆነዋል ። መርህ ግብራችውም አይናርም ። በመዝ አደሩ መርህ ግብር ይተካል ።

ይኸ፣— ከዚህም በቀር በየካቲት ፮፱ አምስቱ የጎቡዕ ድርጅቶች ባወጡት የጋራ መግለጫ ፣ ለሰፊው ሕዝብ የዲሞክራሲን መስፍት አማዳፊነት ተስ ማምተውበት ነበር ።

እንግዲህ እንዳንዶቹ ማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅቶች የዲሞክራሲን ጥያቄ በሚመለከት ረገድ ፣ ከየራሳቸው መርሐ ግብርና በየካቲትም ካወጡት የጋራ መግለጫ ላይ «የአዋም ግሽ ሻል» አድርገው ከሆነ ፣ ይህንን መሻ ሻል ምን አመጣው ነው ? የእኔ ጥያቄ ።

ጦርነቱ ነው እንዳይባል ፣ ፊውዳሊ ዝምን ኢምፔሪያሊዝምና ቢርክራሲ ያዊ ካፒታሊዝምን ለመደምሰስ መለስ ተኛውን ፕሮግራም ስናወጣ ፣ ጦርነት እንደሚከፈትብን አስቀድመን እናው ቀው ነበር ። ከዚህም ጋር በሀገራቱ ተጨባጭ ሁኖቴዎች ላይ የደረሰ ለውጥ ቢኖር ፣ ለዲሞክራሲ መለቀት ሌላው ገጽታ ለሆነው ለዲሲፕሊን እመቹ የሚያደርገው የሕዝባዊና ሌላም ድር ጅቶች ዕድገት ከለምና የተሻሻ ሆኖ መገኘቱ ነው ።

የዲሞክራሲው ጥያቄ ከርከር ሰሞ ኑን እንደተደዘው ዓይነት ሊቀየል ይችላል ። ወይም ሊጸረጥ ይችላል ። ጀዚህን ጥያቄ ያቀረብኩት ቁርጠን ለማወቅ ብቻ ነው ።

አዲስ ዘመን

የጎ አመጽ

ብርሃኑ ዘርይሁን ።

ቅዳሜ ጎሪር ፭፱ ቀን ፲፱፻፸፰ ዓመተ ምሕረት ።

(ርእሰ አንቀጽ)

ሌሎች ም ጉዳዮች

የአኛ ዶክትሪን—ይሳል ኤንግልስ በእርሱና በጠነኛ ጓደኛው ስም—የተግባር መመሪያ እንጂ ቀኖና አይደለም ። ኤንግልስ ጥርት ባለ አኳ ኋን የገለጠው ይህ የማርክሲዝም ዓይነተኛ ቁም ነገር ብዙ ጊዜ ይዘነ ጋል ። በቸልታም ይታለፋል ። ማርክሲዝም እንደቀኖና ሲመለድ ደግሞ የተታመሰና ሕይወት የሌለው በድን ይሆናል ። የቅሬኔ ሕግጋትንና የታ ሪካዊ ዕድገት መሠረቱን ያጣል ። ከእያንዳንዱ ዘመን ጋር ያለው ተግ ባራዊ ግንኙነት ይበጠሳል ። ይህም ሲሆን ጭቁን ሕዝቦች ነፃ የሚወ ጡበት መሣሪያነቱ ዱልዱም ይሆናል ።

ስለዚህም ነው አብዮት የሚያካሒዱ ሕዝቦች ሁሉ ማርክሲዝም ሌኒንዝምን እንደተግባር መመሪያ በመውሰድ ከገዜውና ከተጨባጩ ሁኖቴ ጋር በማናበብ ፣ መመሪያ መንደፍና ታክቲክ መቀየስ ያለባ ቸው ። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብም ፣ በፊውዳሊዝም ፣ በኢምፔሪያሊ ዝምና በቢርክራሲያዊ ካፒታሊዝም ላይ ለሚያካሒደው ትግል ትክክ ለኛ መንገድ መቀየስና ኃይሉን አጠናክሮ ወደፊት መራመድ እንዳለበት ግልጥ ነው ። በእጭሩ የአብዮቱ መሥመር ሙተመንና ጥርጊያው መታ ወቅ አለበት ። ይህ አጠቃላይ መመሪያ ይህ የአብዮታችን ጥርጊያ መሥመር ብሔራዊው ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ነው ። በዚህ ፕሮግራም ውስጥ የአብዮቱ ሠፈርና የአብዮቱ ጠላቶች በሚገባ ተከል ለው ተጠቅሰዋል ። የአብዮቱ ሠፈር ወገኖች በአጠቃላይ በምን አኳ ኋን ተደራጅተውና ተባብረው ጠላታቸውን ድል ነሥተው አዲሲቷን ሕዝባዊት ኢትዮጵያ እንደሚመሠርቱና ወደሶሺያሊስት ጎበረተሰብ እን ደሚሸጋገሩ ተመልክቷል ።

ከፍ ብለን እንደጠቀስነው ይህ እንግዲህ በአጠቃላይ ነው ። ነገር ግን ፕሮግራሙ ቡተግባር ስለመዋሉና ስለሚያጋጥሙት ችግሮች በእ ብዮቱ ሂደት ላይ በየደረጀው ስለሚፈጠሩት ሁኔቴዎች በተራማጀች መኸከል ስለሚፈጠሩት የመሥመር ልዩነቶች ፣ በጎበረተሰቡ መኸከል ስለሚነሱት ጥያቄዎች በየጊዜው መወያየት የጎድ አስፈላጊ ነው ። የአ ዲስ ዘመን ጋዜጣ አብዮታዊ መድረክ ተፋፍሞ እንዲቀጥል ፣ ተራማጅ ቡድኖች ፣ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች አገር ወዳዶች ሁሉ አስተያየታቸ ውን እንዲያቀርቡ የጋበዝነው በዚሁ መንፈስ ነበር ። ስለዚሁ ቡተጻ ፈው ርዕሰ አንቀጽ ላይም በተራማጅ ቡድኖች መኸከል የመሥመር ል ዩ ነት ስለፈጠሩትና የጊዜው የጎበረተሰብ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ስለሆ ኑት ከሞላ ጎደል አርእስቶች መዘርዘራቸው የሚታወስ ነው ። ከአርእ

በተቋቋመ መከከል በተለይ በዲሞክራሲ ጥያቄ ለተቂት ሳምንታት ያህል ውይይት ሲደረግበት ሰንብቷል ። የዲሞክራሲ ጥያቄ የብዙዎቹ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ሁሉ ቁልፍ መሆኑ ቢታመንም የኒዚው አንገብጋቢ ጥያቄ የዲሞክራሲ መብት ያስገደበ መለቀት ብቻ አይደለም ። ስለዚህም በእርሱ ብቻ ከማተኮር በሌሎችም ጉዳዮች የማንወያይበት ምክንያት የለም ። ሌሎች ጉዳዮች በሚነሱበት ጊዜም ከዲሞክራሲ ጋር ባላቸው ግንኙነት ስለዲሞክራሲም መጥቀስ ይቻላል ።

እንደነና ለማስታወስ ያህል ከኒዚው አንገብጋቢ ጥያቄዎች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

የመዝ አደሩ ፓርቲ አመሠራረት ፣
የተራግጀች ጉብረት ፣
የብሔረሰቦች ጥያቄ ፣
የቢርከራሲ ጉዳይ ፣
የሪጅናል አቶኖሚ ጉዳይ ፣
የመዝ አደሩ አምባገነንነት ።

በእነዚህ ጉዳዮች ላይ በየአብየኑ ሠፈር የቀሙ ተራግጀችና ምሁራን ሁሉ እስተያየታቸውን ቢሰነዝሩ አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን ተዛማጀነት እያገናዘቡ ፕሮግራሙን ለማራመድ የሚያስችል ጠቅላላ አመለካከት ለመውሰድ የሚረዳ ሊሆን ይችላል ። ፀረ ፊውዳል ፣ ፀረ ኢም ፔሪያሊስትና ፀረ ቢርከራሲያዊ ኃይሎች ሁሉ በፓርቲዎቻቸውና በሌሎች ድርጅቶቻቸው አማካይነት አብሮቱን ወደፊት ለማራመድ አብዮታዊ ግንባር ፈጥረው አንድነታቸውን በማጠንከር የበላይ ግዥነት ሥልጣናቸውን መጨበጥ የሚቻለው ይህ ጠቅላላ አመለካከት አስቀድሞ ሲገኝ ነው ።

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board

ማሰሰቢያ

ውድ አገባቢያያቻችን፣

የውስጥ ገፅና ቁ ከውስጥ ሆኖ ቦርበር ለማደከም ያደረገው ጫጫራ ስላለ ተከካለት አርሱን ከገፅና ቁያቸን ያገለለው ፀረ ሕዝበ ቡድን ከየርብ ጊዜ ደምሮ፣ከአስር ዓመት በላይ ሰፊው ሕዝበ ጉን በመሰለና ያለማታረፕና ያለመ ታከት ፀረ ኢም ፕሪ ያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት ተገሰ ሲያከ ሄድ በኖረው ማህበራቸገና በነ ዘህም አስር ዓመ ታት ያለ ተሰጠ ፕሙን ነፂነት በመገጠት የሰፊውን ሕዝበ ድምዕና ተገሰ ሲያስ ተጋቡ በኖረት ፣ከ የተናውም የተማሪ ማህበራት መጽሔት በላይ የሰፊው ሕዝበ ግስ ተማሪ ያና መ ቀስ ቀሻ ሆነው በ የዩት በ<u>ታመትና</u> በ<u>ተገሊቸገ</u> ሰም መጠ ነም ደምረ የለ: :
የዘህ ፀረ ሕዝበ ቡድን ዓለማ ማህበራቸገ አገዲሠም <u>ታመት</u>ና <u>ተገሊቸገ</u> በአስር ዓመት ቆራጥ ተገለ ቧተረፈት ሰም ተመትቀ ፀረ ሕዝበ ፖለ ቲካውን ለመሸፈገ ነው: :እገዲሁም ከውስጥ ሆኖ ያታውን የኢት ዬጵያ ተማሪ ያቸና ተራማጀች አገድነት የማናለስ ጫጫራ ከውጭ ሆኖ ወሃገባር በመገዛት ለማፋፋም ነው: :ይህም እገደማይሰካ የተረጋገጠ ነው: :
ለማገናኘም፣ የተለመደው የመጽሔት አዘጋጁ ቦርድ አድራሻ/ግለትም P.O.BOX 3198
10363ካ STOCKHOLM - SWEDEN ያለ ያዙ፣ የዓለም ዓ ተና የኢት ዬጵያ ተማሪ ያች <u>ማህበር</u> አባለ ነትገ የማ ያመለከ ት ገገ የማህበራቸገ መጽ ሄቶች ሰም የያዙ መጽ ሄቶች ወዘተ በአውሮፓ የኢት ዬጵያ ተማሪ ያች ማህበር መጽ ሄቶች አለመሆና ፕሙን እገጽታወቁለገና እገድታስ ታው ቁለገ እገጠይ ታለገ: :ለአ ነዚህ አይ ነት መጽ ሄቶች ተጠ ያቂው ••ባለም ዓ ተና ሬጓሪሽገ •• በሚባለ ሰም የታወ ቁው የነ አስፋወሰገ — መገገሽ ሥ ም የወጣ ቶች ድርጁት ነው: :

ከፋፋ ፃቸና አወናባጆች ከፊውዳሊዝምና ከኢም ፕሪ ያሊዝም ጋር ይውደሙ!
የአውነተኛ አብዮታዊያገና ተራማጆች አገድነት ይ ኸር!
ድሉ የሰፊው ሕዝበ ነው!

በአሊተማ የመጽ ሄት አዘጋጁ ቦርድ